# የቁርአን እና
# የመጽሐፍ ቅዱስ ልዩነት

## (ንጽጽራዊ አቀራረብ)

# 2010

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ባፕቲስት ቤተክርስቲያን

**Ethiopian Evangelical**
**Baptist Church**
2822 S. Jupiter Rd.
Garland, TX 75041
Tel: (214) 703-0100 Fax: (214) 703-0161
WWW.EEBC-DALLAS.ORG



# ከበደ ሞላ

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው!

አንደኛ እትም መስከረም 2001 ዓ.ም
ሁለተኛ እትም ሚያዝያ 2002 ዓ.ም

ክብርና ምስጋና ለእግዚአብሔር፣
መታሰቢያነቷ ደግሞ ስለ ወንጌል
ሰማዕት ለሆኑ ሁሉ!

# ማውጫ

መግቢያ ........................................ 5

## I. ኖህና ቤተሰቡን በሚመለከት

1.1 የኖህ ሚስት የሎጥ ሚስት ዕድል እንደ ገጠማት ........ 8
1.2 ኖህ ከሐዲዎችን እንዳይተው በእግዚአብሔር ስለ መናገሩ ........ 8
1.3 ከኖህ ልጆች መካከል አንዱ በጥፋት ውኃ ጊዜ ስለ መስጠሙ ........ 9
1.4 የኖህ መርከብ ጁዲይ በሚባል ተራራ ላይ ስለ ማረፉ ........ 10

## II. አብርሃም፣ ሎጥና እስማኤልን በሚመለከት

2.1 አብርሃም የቤተሰቡን ጣዖታት ስለ መሰባበሩ ........ 11
2.2 አብርሃም በተጠራ ጊዜ አባቱን ተከተለኝ ስለ ማለቱ ........ 11
2.3 አብርሃም ለአባቱ ለመጸለይ ቃል ስለ መግባቱ ........ 12
2.4 የአብርሃም አባት አዘር ስለ መባሉ ........ 12
2.5 እስማኤል ነቢይ ነው ስለ መባሉ ........ 13
2.6 አብርሃምና እስማኤል ካዕባን ስለ መገንባታቸው ........ 13
2.7 ሎጥ የሰዶም ሰዎች ሁሉቱን ሴት ልጆቹን እንዲያገቡአቸው ስለ መጠየቁ ........ 14
2.8 የሎጥ ሚስት የጨው ዓምድ ሆና እንደምትቀር መላእክት አስቀድመው ስለ መናገራቸው ........ 15

## III. ሙሴ፣ አሮን፣ ፈርዖንና ሐማን በሚመለከት

3.1 ሙሴ አሮንን ወደ ፈርዖን እንዲልከው በእግዚአብሔር ስለ መናገሩ ........ 16
3.2 የፈርዖን አስማተኞች ገመዶች እንደጣሉ ........ 16
3.3 ሙሴ በትሩን ጥሎ እባብ በሆነች ጊዜ ሸሽቶ አለመመለሱ ........ 16
3.4 ፈርዖን ሐማን ግንብ እንዲያሠራለት ስለ መጠየቁ ........ 17
3.5 ሙሴ ዮቶርን ለሚስት ብሎ ለስምንት ዓመት ስለ ማገልገሉ ........ 18
3.6 ሙሴ ወደ ፈርዖን፣ ሐማና ቆሬ ስለ መላኩ ........ 19
3.7 ፈርዖን ሙሴን ለመግደል ስለ መዛቱ ........ 20
3.8 ሙሴ በግብጽ ዘጠኝ ተአምራት ብቻ ስለ ማድረጉ ........ 20
3.9 ሙሴ ኢያሱ እንዲያስተምረው ስለ መጠየቁ ........ 21
3.10 ሙሴ እግዚአብሔር በተገለጠለት ጊዜ ቤተሰቦቹን እዚህ ቆዩ ስለ ማለቱ ........ 21
3.11 ሙሴ የፍየሎች እረኛ እንደነበረ ........ 22
3.12 አሮንን ሙሴ ራሱ ስለ መምረጡ ........ 22
3.13 ፈርዖን አስማተኞችን በስቅላት ሊቀጣቸው ስለ መዛቱ ........ 23
3.14 ሙሴ ድንጋዩን በመታው ጊዜ አሥራ ሁለት ምንጮች ስለ መፍሰቃቸው ........ 23
3.15 ሙሴ፣ አሮን፣ የወርቅ ጥጃውና አል - ሳምራዊው ........ 24

## IV. *ያዕቆብና ልጆቹን በሚመለከት*

4.1 ያዕቆብ ልጁ ዮሴፍ ሕልሞቹን ለወንድሞቹ እንዳይናገር ስለ ማስጠንቀቁ ....................25
4.2 ስለ ዮሴፍና የጲጥፋራ ሚስት ....................25
4.3 የዮሴፍ ወንድሞች አባታቸው ዮሴፍን ወደ እነርሱ እንዲልክ ስለ መጠየቃቸው ....................25

## V. *ንጉሥ ሰለሞንን በሚመለከት*

5.1 ከሰይጣናት መካከል የንጉሥ ሰለሞን አገልጋዮች እንደሆኑ ....................27
5.2 ንጉሥ ሰለሞን ከወፎች ጋር የመነጋገር ችሎታ ነበረው ....................27
5.3 የንጉሥ ሰለሞን ሠራዊት ጋኔኖችና ወፎች ነበሩ ....................28
5.4 ጉንዳኖች እርስ በርስ ሲነጋገሩ ንጉሥ ሰለሞን ይሰማቸው ነበር ....................28
5.5 ሁድ ሁድ የተባለ ወፍ ለንጉሥ ሰለሞን ምስጢር ስለ መናገሩ ....................28
5.6 ሁድ ሁድ ለሳባ ንግሥት መልዕክት ስለ ማድረሱ ....................29

## VI. *ኢየሱስ ክርስቶስን በሚመለከት*

6.1 በዘምባባ ዛፍ ሥር ስለ መወለዱ ....................30
6.2 በሕፃንነቱ እንደ ትልቅ ሰው ስለ መናገሩ ....................30
6.3 ከጭቃ ወፍ መፍጠር ስለ መቻሉ ....................31
6.4 ሰዎች በቤታቸው የሚመገቡትን ስለ ማወቁ ....................31
6.5 አለመሰቀሉና አለመሞቱ ....................32
6.6 እግዚአብሔር ልጅ እንዳልወለደ ....................32

## VII. *ሌሎች ነጥቦች*

7.1 የሲና ተራራ በእስራኤል ሕዝብ ላይ ስለ መንሳፈፉ ....................33
7.2 ሕይወት ያላቸው ሁሉ ከውኃ ስለ መፈጠራቸው ....................33
7.3 ሰው ችኩልና ደካማ ሆኖ ስለ መፈጠሩ ....................34
7.4 ስለ ነነዌ ከተማ የሕዝብ ብዛት ....................35
7.5 እግዚአብሔር መላእክትን ስለ መውለዱ ....................35
7.6 ምድር በሁለት ቀናት እንደ ተፈጠረ ....................36
7.7 ስለ ቃየል፣ አቤልና የቁራ ሚና ....................36
7.8 መንፈስ ቅዱስ ገብርኤል ስለ መባሉ ....................37
7.9 ሰይጣን ከሰማይ የተጣለው ለአዳም ባመስገዱ እንደሆነ ....................38
7.10 ዘካርያስ ሦስት ቀንና ሌሊት ብቻ መናገር አለመቻሉ ....................39
7.11 የሳኦል ሠራዊት በውኃ ስለ መፈተኑ ....................39
7.12 ድንግል ማርያም የሙሴና የአሮን እህት ስለ መባሏ ....................40


# የቁርአን እና የመጽሐፍ ቅዱስ ልዩነት

## መግቢያ

ቁርአን ወይም ፉርቃን በመባል የሚታወቀው መጽሐፍ ለእስልምና ሃይማኖት መሰከታዊና የጠራ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ይታመናል:: በመሆኑም ቁርአን 114 ሱራዎች (ምዕራፎች) ሲኖሩት፣ በ30 ጁዝእ (ክፍል) ተከፍሎ፣ 6,236 አያት (አንቀጾች) ወይም ቁጥሮች አሉት:: በርካታ ሙስሊሞች አረብኛ ቋንቋ አወቁ አላወቁ፣ ትርጉሙን ተረዱ አልተረዱ ከሕፃንነታቸው ጀምረው ቁርአንን በአረብኛ እንዲማሩና እንዲያጠኑ ይደረጋል:: በዚሁ ዓይነት ሁኔታ 30ውም ጁዝእ ከመጀመሪያው ጀምረው እስከ መጨረሻው ድረስ በቃላቸው የሚያነበንቡ በርካቶች ናቸው::

ቁርአን በገብርኤል አማካኝነት በመሐመድ ላይ መውረድ ጀመረ ተብሎ የሚታመነው በ610 እ.ኤ.አ እንደሆነ እስላማዊ ምንጮች ይጠቁማሉ:: መሐመድ ማንበብና መጻፍ የማይችል ስለሆነ «ሂራዕ» በሚባል ዋሻ ውስጥ ሆኖ የተቀበላቸውን አዳዲስ መገለጦች በአእምሮው በመያዝ መጻፍ የሚችሉትን (የተማሩትን) ሰዎች ገብርኤል እንዲህና እንዲህ አለኝ በማለት እየነገራቸው ያስጽፋቸው እንደነበር ይታመናል:: በመሆኑም መሐመድ ሌሎች ሰዎችን ማስጻፉን የሚከተሉት የቁርአን አንቀጾች ያረጋግጣሉ (አል - ፉርቃን 5፤ አል - አዕራፍ 158)::

ቁርአን የወረደው ወይም የተገለጠው ለ23 ተከታታይ ዓመታት መካከል እንደሆነ ይነገራል:: ይህም መሐመድ ከዚህ ዓለም በሞት እስኪለይ ድረስ ማለት ነው:: ጊዜውም ከ610 እስከ 632 እ.አ.አ መሆኑ ነው:: መገለጡም ደግሞ የተቋረጠው መሐመድ ሲሞት ነው:: ምናልባት መሐመድ ከዚህ ዓለም በሞት ባይለይ ኖሮ መገለጡ ይቀጥል ወይም አይቀጥል እንደሆነ የሚታወቅ ነገር የለም:: ስለ ቁርአን ምንጭ፣ አደረጃጀትና ይዘት በተመለከተ እስላማዊ ምንጭ በሚከተለው ዓይነት ሁኔታ ያስረዳል:: ይኸውም:-

> *«ቅዱስ ቁርአን በብራናም በሰሌዳም በአጥንትም በሰሌንም በሰላ ድንጋዮችም ላይ የአያቶቹ ተራ ተጠብቆ ተጽፎ በነቢዩ ቤት ይቀመጥ ነበር፤ ብዙዎች ምዕመኖች በቃላቸው አጥንተው ሲኖሩ ከነቢዩ እረፍት በኋላ በ12ኛ ዓመተ ስደት በየማማህ በተደረገው ጦርነት በቃላቸው ካጠኑት ብዙዎቹ ስለ አለቁ እንዳይጠፉ በመስጋት በዑመር አልኸጠብ አስታዋሽነት አቡበከር አልሲድቅ ዘይድ ሣቢትን አዘው ጽሑፎቹንና በቃል ያጠኑትን እያመሳከረ የአያቶቹን ተራ ጠብቆ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ በአንድ ጥራዝ ሰበሰበው:: ስም አውጡለት ተብሎ ገሚሶቹ ሲፍር ይባል ቢሉ ይህ የአይሁድ አጠራር መኾኑን ጠልተው የሐበሻ (ኢትዮጵያ) ሰዎች መሰሉን መጽሐፍ ይሉታል በማለት መጽሐፍ ብለው ጠሩት ማለትን ኢትቃን በ1.89 ገጽ ላይ ያስረዳል::*

> *«ዳግመኛ ኸሊፋ ዑስማን በ25ኛው ዓመተ ስደት ባነባበቡ ግጭት ስለተገኘ በአራት የቁርአን ሊቃውንት በተከናወነ ጉባኤ የቃላቱን አጻጻፍ ያለ ነጥብ ለንባብ ተስማሚ አድርገው በመጀመሪያው አወራረድ መሠረት የሱራዎቹንም ተራ ጠብቀው ሰበሰቡት፤ ኸሊፋውም በአምስት ኮፒዎች*

*አስጸፎ አንዱን ለራሱ አስቀርቶ አራቱን እንዲገለበጥ አድርጎ የቀረውን ስለ አ.ቃጠለው ቁርአን አንድነቱን ጠብቆ ይኖራል። እስከ አሁን ምንም መለወጥ አልደረሰበትም። ቁርአን ሁለት አወራረድ አለው። መጀመሪያ ከተጠበቀው ሰሌዳ በቅርቢቱ ሰማይ ወደሚገኘው ወደ ልቅናው ቤት በረመዳን ወር በከፍተኛይቱ ሌሊት በአንድ ጊዜ ለጂብሪል ወርዷል። የመጽሐፉም ተራ አቀማመጥ በዚሁ ዓይነት ነው።*

*«ሁለተኛ አወራረድ በጂብሪል አማካይነት በነቢዩ መሐመድ ላይ በ23 ዓመታት ውስጥ እንደ አስፈላጊነቱ እየተከፈለ ነው። በዚህ መሠረት መካዊና መዲናዊ በመባል ተከፍሏል። ክፍያውም ጊዜን እንጂ በፍራን አይመለከትም...»*[1]።

በእንጻሩ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው በ1500 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ሲሆን፣ የክርስትና መሰኮታዊ መጽሐፍ ነው። በመሆኑም መጽሐፍ ቅዱስ ከቁርአን በፊት የ2000 ዓመታት ያህል ርቀት አለው ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በመሰኮታዊ ምሪት በር የመጻፉ አንዱና ጠንካራው መረጃ በመልዕክቶቹ ውስጥ ያለው አንድነት ነው። ምንም እንኳን ጸሐፊዎቹ ከተለያየ ተሞክሮ ቢመጡም፣ ሁሉም አንድ ዓይነት ፅንሰ ሐሳብና መርህ ይጋራሉ። መጽሐፍ ቅዱስ በነገሥታት፣ በእረኞች፣ በዓሣ አጥማጆች፣ በካህናት፣ በቀረጥ ሰብሳቢ፣ በሐኪም እንዲሁም በተለያየ የሥራ ዘርፍ በተሰማሩ አርባ ያህል ሰዎች ቢጻፍም፣ መልዕክቱን የተቀበሉት ግን ከአንድ ምንጭ ከእግዚአብሔር መሆኑን መላው ክርስቲያኖች ይስማሙበታል። ስለሆነም የክርስትና መሰኮታዊ መጽሐፍ (መጽሐፍ ቅዱስ) በሁለት ይከፈላል። እነዚህም ብሉይና አዲስ ኪዳን በመባል ይታወቃሉ። የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ብዛት 39 ሲሆኑ 929 ምዕራፎች አሉት። የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ብዛት ደግሞ 27 ሲሆኑ 260 ምዕራፎች አሉት። በአጠቃላይ ሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ 1,189 ምዕራፎች ያሉት ሲሆን፣ ለመቁጠር የሚያዳግት በርካታ አንቀጾች ወይም ቁጥሮች አሉት።

በቁርአን የሚገኙ ታሪኮች በርካታዎቹ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ተመሳሳይነት አላቸው። ሆኖም በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተጻፉት ይለያያሉ። ለምሳሌ፦ የዮናስ፣ የዮሴፍ፣ የአብርሃም፣ የማርያም ምዕራፎች (ሱራዎች) በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። የሙሴ፣ የአሮን፣ የኖህ፣ የዳዊት፣ የሰለሞንና የሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ምዕራፍ ባይሰጣቸውም ታሪካቸው በቁርአን ይገኛል።

በመሆኑም ይህች ጽሑፍ የተዘጋጀችው ቁርአንን ለመተርጎም፣ ለማብራራትና ለመተቸት፣ ወይም ደግሞ ቁርአን የእግዚአብሔር ቃል ነው ወይስ አይደለም? ወደ ሚለው አተካራና ሙግት ውስጥ ለመግባትም አይደለም። ነገር ግን የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ በመጽሐፍ ቅዱስ እና በቁርአን የሚገኙ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ምን ያህል እንደሚለያዩ ለአንባቢያን በቀላሉ ለማስጨበጥ የቀረበ ንጽጽራዊ አቀራረብ ነው። ስለሆነም አንባቢያን መጽሐፉን ካነበቡ በኋላ የትኛው እውነተኛ ታሪክ እንደሆነና እንዳልሆነ የግላቸውን ውሳኔ ወይም አስተያየት መስጠት ይችላሉ።

የቁርአንን ምንጭ ወይም አወራረድ በተመለከተ ለመግለጽ ያስፈለገበት ምክንያት፣ በተለይ ክርስቲያኖች ስለ ቁርአን መጠነኛ ግንዛቤ እንዲያገኙ ሆኖ፣

1. የቁርአን መቅድም ገጽ 9 እና 10



ከቁርአን ጋር ለመተዋወቅ ለሚሹ የወንጌል አገልጋዮች ደግሞ እንደመነሻ ሆኖ ሊጠቀሙባቸው እንደሚችል ታስቦ ነው። ከዚህም ባሻገር ክርስቲያኖች ከሙስሊም ወዳጆቻቸው ጋር በየአጋጣሚው ሲገናኙ በመጽሐፍ ቅዱስ የሌለ ታሪክ እንዴት በቁርአን ሊኖር ቻለ? ብለው መጠየቅና ሰላማዊ ወይይት ማድረግ ይችላሉ። ምክንያቱም ቁርአን የተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ (ብሉይና አዲስ ኪዳን) ተጽፎ ካበቃ ከ500 ዓመታት በኋላ ስለሆነ ነው።

እንግዲህ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ክርስቲያን እንደመሆኑ መጠን ወገንተኝነት ሳያጠቃው ገለልተኛ አቋም በመያዝ ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ብቻ በቁርአንና በመጽሐፍ ቅዱስ መካከል ያለውን እጅግ ሰፊ ልዩነት በንጽጽር ለማቅረብ ሞክሮአል። በመሆኑም ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች መጽሐፉን ካነበቡ በኋላ ልዩነቶቹ በምን ምክንያት ሊከሰቱ እንደቻሉ ከዚህ በበለጠ ሁኔታ ማጥናት እንደሚችሉ ይታመናል።

ስለሆነም መጽሐፉን በተገቢው መንገድ ለማንበብና ለማጥናት ያመች ዘንድ በምዕራፍ ተከፍሎአል። ይህም የጽሑፉን መሠረተ ሐሳብ በቀላሉ ለመረዳትና ለመጨበጥ ያስችላል። ስለሆነም ኖህና ቤተሰቡን፣ አብርሃም፣ ሉጥና እስማኤልን፣ ሙሴ፣ አሮን፣ ፈርዖንና ሐማን፣ ያዕቆብና ልጆቹን፣ ንጉሥ ሰለሞንን፣ ኢየሱስ ክርስቶስን እና ሌሎች ነጥቦችን በሚመለከት በቁርአን እና በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኙ ተመሳሳይ ታሪኮች ምን ያህል እንደሚለያዩ የሚገልጹና የሚያብራሩ ሃምሳ አራት ነጥቦች በዚህ ጽሑፍ ቀርበዋል።

መልካም ንባብ!

ኪ.ም

# I. ኖህና ቤተሰቡን በሚመለከት

## 1.1 የኖህ ሚስት የሉጥ ሚስት ዕድል እንደ ገጠማት

*«አላህ ለነዚያ ለካዱት ሰዎች የኑሕን ሴትና የሉጥን ሴት ምሳሌ አደረገ፤ ከገቢዎቹም ጋር አሳትን ግቡ ተባሉ»* (ቁርአን ሱረቱ 66÷10)::

የሉጥ ሚስት ባለመታዘዝዋ ምክንያት የጨው አምድ ሆና እንደ ቀረች መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል:: ነገር ግን የኖህ ሚስት የሉጥ ሚስት ዕጣ ወይም ዕድል እንደ ገጠማት ከመጽሐፍ ቅዱስ ማረጋገጫ አይገኝም:: በጥፋት ውኃ ጊዜ ወደ መርከብ ገብተው የዳኑት የኖህ ሚስት፣ ሦስቱ ወንድ ልጆቹና የልጆቹ ሚስቶች፣ በጠቅላላው ስምንት ሰዎች ከጥፋት ውኃ አደጋ እንደ ዳኑ መጽሐፍ ቅዱስ ከመናገር ውጪ ከቁርአን ጋር የሚመሳሰል ታሪክ አላቀረበም (ዘፍጥ. 7÷7፤ 1 ጴጥ. 3÷20)::

በመሆኑም የኖህ ሚስት ጥፋት ምን እንደሆነ ቁርአን አይናገርም:: በመሠረቱ ምንም ዓይነት ጥፋት ሳይኖርባት ወደ እሳት መግባቷ ግልጽ አይደለም:: የሉጥ ሚስት መለከታዊውን ማስጠንቀቂያ በመጣሷ ምክንያት ውጤቱ የጨው አምድ ሆና መቅረት ሆነ:: ታዲያ ስለ ኖህ ሚስት በተመለከተ ቁርአንና መጽሐፍ ቅዱስ ያቀረቡት ታሪክ የተለያየ ከሆነ የማንን ነው መቀበል የሚገባን?

## 1.2 ኖህ ከሐዲዎችን እንዳይተው ለእግዚአብሔር ስለ መናገሩ

*«ኑህም አለ፡- ጌታዬ ሆይ! ከከሐዲዎቹ በምድር ላይ አንድንም አትተው»* (ቁርአን ሱረቱ 71÷26)::

በኖህ ዘመን ከሰዎች ኃጢአትና ክፋት የተነሳ ምድር የተበላሸች እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ዘፍጥ 6÷5,13):: ነገር ግን በዘመኑ ከነበሩት ሰዎች መካከል ኖህ ብቻ ጻድቅ እንደ ነበር ተመስክሮለታል:: ከዚህ የተነሳ ኖህ በታላቅ እምነቱ ምክንያት ከእምነት አርበኞች ተርታ ሊመደብ ችሏል (ዕብ. 11÷7):: እግዚአብሔር የዓለምን ኅብረተሰብ በጥፋት ውኃ እንደሚያጠፋቸው ከተነገረው ጊዜ ጀምሮ ኖህ ሕዝቡ ዐመጻቸውን ትተው ወደ እግዚአብሔር ይመለሱ ዘንድ በፍቅርና በትጋት ይሰብክ እንደነበረ ሐዋርያው ጴጥሮስ በመልዕክቱ ገልጾአል (2 ጴጥ. 2÷5)::

ከዚህ ሌላ ቁርአን ላይ ያለው ሐሳብ ኖህ ከሐዲዎችንና ዐመጸኞችን እግዚአብሔር እንዲያጠፋቸው ወይም እንዳይተዋቸው በእግዚአብሔር የተናገረበት አጋጣሚ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አይገኝም:: ይሁንና ግን እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ መሠረት ኅብረተሰቡ ንስሐ ገብተው በመመለስ ከእርሱ ጋር በመተባበር ከጥፋት ውኃ የሚድኑበትን መርከብ እንዲያዘጋጁ እየጋበዘ፣ ለእነርሱ ጥፋት መመኘቱ እንዴት ይታያል? ታዲያ ማመን የሚገባን የመጽሐፍ ቅዱስን ወይስ ቁርአን ያቀረበውን ታሪክ ነው?



## 1.3 ከኖህ ልጆች መካከል አንዱ በጥፋት ውኃ ጊዜ ስለ መስጠሙ

*«ልጁም፡- ከውኃ ወደ ሚጠብቀኝ ተራራ እጠጋለሁ አለ፤ (አባቱም)፡- ዛሬ ከአላህ ትእዛዝ ምንም ጠባቂ የለም፤ (እርሱ) ያዘነለት ካልሆነ በቀር አለው፤ ማዕበሉም በመካከላቸው ጋረደ፤ ከሰጣሚዎቹም ኾነ»* (ቁርአን ሱረቱ 11÷43)::

ቁርአን በጥፋት ውኃ ጊዜ ከኖህ ልጆች መካከል አንዱ በውኃ ሰጥሞ እንደ ሞተ ይናገራል:: ሙስሊም ተንታኞችም ከላይ ያለውን የቁርአን አንቀጽ እንደሚከተለው ተንትነውታል፡-

*«የጥፋት ውኃ ከጀመረ በኋላ ኖህ ልጃቸውን አስታወሱና የአባትነት ስሜታቸው ገፋፍቶአቸው አብረዋቸው ከተሳፈሩት ቤተሰቦቻቸው ጋር እንዲሳፈር ጠሩት:: ልጁ በከሐዲነት አቋሙ የፀና ስለ ነበር ከመርከቧ ርቆ ይገኝ ነበር፡፤ አባቱም እንዲህ አሉት፡- 'ልጄ ሆይ ሰጥመህ እንዳትጠፋ ና ከኛ ጋር ተሳፈር ከከሐዲዎቹና የአላህን ኃይማኖት ከተውት ሰዎች ጋር አትሁን':: ነገር ግን ልጁ ለጥሪአቸው ምላሽ አልሰጠም:: በኃጢአት አቋሙ ፀና:: ያተከሰተው ነገር በተፈጥሮ የተለመደ ጉዳይ ነው የሚል ግምት አደረበት:: መርከቧንም ሳይሳፈር የሚድን መሰሉ ታየው:: ለአባቱም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፡- 'ውኃ ወደ ማይደርስበት ጎራ ወጥቼ ከአደጋው እድናለሁ':: አባቱም፡- 'አላህ በካዱ ወገኞች ላይ ከወሰነው ቅጣት የሚያድን አንድ ኃይል የለም አሉት':: ልጁ አባቱ የሚነግሩትን ሊሰማ አልቻለም:: ወደ ጎራው ለመውጣት ያቀደው ሐሳብ ያድነኛል የሚል እምነት አደረበት:: ነገር ግን የካደውንና የጠመመውን ልጅ የውኃውና የማዕበሉ ኃይል ለመቅጸበት ወሰደው»*[2]::

እንግዲህ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ ኖህ ሦስት ወንድ ልጆች ነበሩት:: ስማቸውም፡- ሴም፣ ካምና ያፌት ይባላሉ:: እነዚህ ከጥፋት ውኃ በኋላ የትውልድ ሁሉ መገኛ ወይም ምንጭ እንደ ሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ዘፍጥ. 10):: ነገር ግን ቁርአን ከመጽሐፍ ቅዱስ በተቃራኒ በጥፋት ውኃ ጊዜ ከኖህ ልጆች መካከል አንዱ በውኃ እንደ ሰጠመ ይናገራል:: ከላይ ለመመልከት እንደቻልነው የኖህ ልጆች ሦስት ወንድ ልጆች እንደ ነበሩ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጾአል:: እነዚህ የጥፋት ውኃ ሳይጀምር ወደ መርከቡ ከመላው ቤተሰባቸው ጋር የገቡ ሲሆን፣ ውኃው ከምድር ላይ ሲጎድልም ደግሞ ከመርከቡ አብረው እንደ ወጡ ከመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት ይቻላል::

ታዲያ ለመሆኑ ሰጠመ የተባለው ልጅ ማን ይሆን? ሁለቱ መጻሕፍት ያቀረቡት ታሪክ የተለያየ ከሆነስ መቀበል የሚገባን የቁርአንን ወይስ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ ነው?

2. ገድለ ነቢያት በቁርአን ክፍል አንድ መጽሐፍ፤ ደራሲ ዓፊፍ ዓብዱልፈታህ ጠበራ፤ ትርጉም፡- አወል ረታ ሀምዛ 1985 አዲስ አበባ ገጽ 74

## 1.4 የኖህ መርከብ ጁዲይ በሚባል ተራራ ላይ ስለ ማረፏ

*«ተባለም:- ምድር ሆይ ውኃሽን ዋጪ፤ ሰማይም ሆይ (ዝናምሽን) ያዢ፤ ውኃውም ሠረገ፤ ቅጣቱም ተፈጸመ፤ ጁዲይ በሚባልም ተራራ ላይ(መርከቢቱ) ተደላደለች፤ ለከሐዲዎችም ሰዎች ጥፋት ተገባቸው (ጠፉ) ተባለ»* (ቁርአን ሱረቱ 11÷44)::

ከጥፋት ውኃ በኋላ የኖህ መርከብ *'አራራት'* በሚባለው ተራራ ላይ እንዳረፈች መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ዘፍጥ. 8÷4):: ተራራውም በዛሬው ዘመን በቱርክ አገር እንደሚገኝ ታውቋል:: ቁርአን ደግሞ የኖህ መርከብ ጁዲይ በሚባል ተራራ ላይ እንዳረፈች ይናገራል:: ሆኖም *'ጁዲይ'* እና *'አራራት'* አንድ ስለ መሆናቸው ምንም የተረጋገጠ ነገር የለም::

ስለሆነም ቁርአን የኖህ መርከብ በጁዳይ ተራራ ላይ አረፈች ካለና መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ የኖህ መርከብ በአራራት ተራራ ላይ እንዳረፈች ከተናገረ እውነተኛ ታሪክ ነው ብለን መቀበል የምንችለው የትኛውን ነው? ለመሆኑ ጁዲይ የሚባል ተራራ በዛሬ ዘመን የት እንደሚገኝ ይታወቃልን??



# II. አብርሃም፣ ሉጥና እስማኤልን በሚመለከት

## 2.1 አብርሃም የቤተሰቡን ጣዖታት ስለ መሰባበሩ

*«(ዘወር ሲሉ) ስብርብሮችም አደረጋቸው፤ ለነሱ የኾነ አንድ ታላቅ (ጣዖት) ብቻ ሲቀር ወደርሱ ይመለሱ ዘንድ (እርሱን ተወው)»* (ቁርአን ሱረቱ 21÷58)::

ይህ የቁርአን አንቀጽ የሚናገረው አብርሃም የቤተሰቡን ጣዖታት ሰባብሮ ከጥቅም ውጪ እንዳደረጋቸው የሚገልጽ ነው:: እንደ ቁርአን አገላለጽ አብርሃም ይህን እርምጃ መውሰድ የቻለው ቤተሰቡን በጽኑ መርምሮአቸው በስህተት ውስጥ እንዳሉ ከተረዳ በኋላ እንደሆነ ቁርአን ተጨማሪ መግለጫ ይሰጣል (ሱረቱ 21÷52-57)::

*ሥ*ልጣን ያላቸው የቁርአን ተርጓሚዎች ይህን በተመለከተ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ይሰጣሉ:: ከእነዚህም መካከል አብርሃም የአገሬውን ሕዝብ ጣዖታት ከሰባበረ በኋላ ወዲያው ተከሶ ፍርድ ቤት ቀርቦ፣ በእሳት ተቃጥሎ እንዲሞት ተፈርዶበት ሳለ እግዚአብሔር በአስደናቂ ተአምር ከእሳት ከመቃጠል አዳነው የሚል ታሪክ ይገኛል:: በእርግጥ አብርሃም እንዲህ ዓይነት እርምጃ ወስዶ ከሆነ ለእውነተኛ አምላክ ከመቅናቱ የተነሳ በመሆኑ ትክክለኛ እርምጃ ወስዶአል ብለን መገመት እንችላለን:: ነገር ግን አስገራሚው ነገር አብርሃም ሌሎች ጣዖታትን ሰባብሮ ካስወገዳቸው በኋላ ትልቁን ጣዖት ለምን እንዳስቀረ አለመታወቁ ነው::

ሌላው ደግሞ አብርሃም ወሰደ የተባለው እርምጃ ታሪኩ በመጽሐፍ ቅዱስ አለመኖሩ ሌላው መሠረታዊ ነጥብ ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ የአብርሃም ታሪክ የሚጀምረው በኦሪት ዘፍጥረት 11÷26-32 ሲሆን፣ ዘፍጥረት 12 ደግሞ አብርሃም በካራን ከቤተዘመዶቹ ጋር ሳለ፣ እግዚአብሔር እንደ ጠራው የሚናገር ክፍል ነው:: በመሆኑም ቁርአን የአብርሃምን እርምጃ ከላይ በተገለጸው መሠረት ያስተምራል:: ሆኖም እንዲህ ዓይነት ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የለም:: መቼም ቢሆን በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሁለት የተለያየ ዘገባ ሲቀርብ ሁለቱም እውነት ናቸው ማለት አይቻልም::

*ታዲያ* ትክክለኛው *ታሪክ* የመጽሐፍ ቅዱስ ወይስ የእስልምና መለኮታዊ መጽሐፍ የሆነው የቁርአን ነው? ልብ ይበሉ! መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ ተጽፎ ካበቃ ከ500 ዓመታት በኋላ ነው ቁርአን የተጻፈው::

## 2.2 አብርሃም በተጠራ ጊዜ አባቱን ተከተለኝ ስለ ማለቱ

*«አባቴ ሆይ! እኔ ከዕውቀት ያልመጣልህ ነገር በእርግጥ መጥቶልኛልና ተከተለኝ፤ ቀጥተኛውን መንገድ እመራሃለሁና»* (ቁርአን ሱረቱ 19÷43)::

ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 12÷1-3 አብርሃም የተጠራበት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስለ መሆኑ ከላይ ከፍ ብሎ ተመልክተናል። አብርሃም እግዚአብሔር በጠራው ጊዜ ወዴት እንደሚሄድ ሳያውቅ በእምነት ብቻ ለእግዚአብሔር ጥሪ ምላሽ ለጥቶ አገሩንና ቤተ ዘመዶቹን (አባቱን ጭምር) ትቶ መውጣቱን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።

ነገር ግን ከዚህ ውጪ አብርሃም አባቱን ተከተለኝ ማለቱ ይቅርና የሎጥ ከእርሱ ጋር መውጣት እንኳን የእግዚአብሔርም የአብርሃምም ፈቃድ እንዳልነበረ እንገነዘባለን። ምክንያቱም ከመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት እንደሚቻለው:- *'ሎጥም ከእርሱ ጋር ሄደ'* የሚል እንጂ *'እግዚአብሔር ሎጥን ጠራው'* የሚል አናገኝም (ዘፍጥ. 12÷4)። በመሆኑም አብርሃም አባቱን ማስከተሉን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማረጋገጫ የለም። ታዲያ ትክክለኛ ታሪክ አድርገው የሚቀበሉት ቁርአን ያቀረበውን ወይስ መጽሐፍ ቅዱስ ያቀረበውን ታሪክ ነው?

## 2.3 አብርሃም ለአባቱ ለመጸለይ ቃል ስለ መግባቱ

*«፡- ደህና ሁን፤ ወደ ፊት ከጌታዬ ምህረትን እለምንልሃለሁ፤ እርሱ ለኔ በጣም ርኅሩህ ነውና አለ»* (ቁርአን ሱረቱ 19÷47)።

እግዚአብሔር አብርሃምን በጠራው ጊዜ አባቱን ተከተለኝ ስለ ማለቱ ቁርአን የገለጸውን ሐሳብ ከላይ አይተን ነበር። በዚህኛው የቁርአን አንቀጽ ደግሞ አብርሃም አባቱን ሲሰናበትና ከእግዚአብሔር ምሕረት ሊጠይቅለት ቃል እንደ ገባለት እናያለን። ታዲያ እነዚህን ሁለት የቁርአን አንቀጾችን እንዴት ማስታረቅ ወይም ማስማማት ይቻላል? አብርሃም አባቱን አስከተለው ወይስ ተሰናበተው? እነዚህ ሁለቱ የቁርአን አንቀጾች እርስ በርስ እንደ ሚጋጩ መገንዘብ ይቻላል። ምክንያቱም ቁርአን ሱረቱ 19÷43 አብርሃም አባቱን ሲያስከትል፣ ቁርአን ሱረቱ 19÷47 ደግሞ አብርሃም አባቱን ሲሰናበት እናያለን።

ስለሆነም አብርሃም ለአባቱ ምሕረት ለመለመን ቃል እንደ ገባለት የሚገልጽ ሐሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ በአንድም ሥፍራ አልተጠቀሰም። ታዲያ ሁለቱ መጻሕፍት ያቀረቡት ታሪክ የተለያየ ከሆነ አስተማማኝና ተአማኒነት ያለው መጽሐፍ የትኛው ነው ብለው ይገምታሉ?

## 2.4 የአብርሃም አባት አዘር ስለ መባሉ

*«ኢብራሂምም ለአባቱ ለአዘር ጣዖታትን አማልክት አድርገህ ትይዛለህን?* (ቁርአን ሱረቱ 6÷74)።

ይህ የቁርአን አንቀጽ ስለ ሁለት ነጥቦች ይናገራል። እነዚህም:- የመጀመሪያው የአብርሃም አባት አዘር ስለ መባሉና ሁለተኛው ደግሞ አብርሃም አባቱን 'ጣዖታትን አማልክት አድርገህ ትይዘዋለህን?' ብሎ መጠየቁን ወይም መውቀሱን ነው። ነገር ግን እንደ ኦሪት ዘፍጥረት 11÷26 አገላለጽ የአብርሃም አባት ታራ ይባል ነበር። ቁርአን ደግሞ የአብርሃም አባት አዘር ነው ይላል። ታዲያ የአብርሃም አባት አዘር ወይስ ታራ ነው?



## 2.5 እስማኤል ነቢይ ነው ስለ መባሉ

*«በመጽሐፉ እስማኤልንም አውሳ፤ እርሱ ቀጠሮን አክባሪ ነበረና፤ መልክተኛ ነቢይም ነበር»* (ቁርአን ሱረቱ 19÷54)።

በመጽሐፍ ቅዱስ እስማኤል የታወቀ ታሪክ ያለው ሰው ነው። የሣራ አገልጋይ የነበረች አጋር የምትባል ሴት ለአብርሃም የወለደችለት ልጅ ነው። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ እስማኤል የተወለደው እንደ እግዚአብሔር የተስፋ ቃል መሠረት አልነበረም። እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለሣራ የገባላቸውን የተስፋ ቃል ባዘገየ ጊዜ አብርሃምና ሣራ ተስፋ በመቁረጣቸው ምክንያት ሣራ ወደ አጋር እንዲገባ መከረችው። ምክንያቷም የልጅ ጥማት ስለ ነበራት ነው። በዚህ መሠረት አብርሃም ወደ አጋር ገባ፤ እስማኤልም ተወለደ (ዘፍጥ. 16÷1-2)።

አብርሃም እምነቱ እንደ በፊቱ ጠንካራና ብርቱ ቢሆን ኖሮ ወደ አጋር ባልገባም ነበር ብለን መገመት እንችላለን። ምክንያቱም እግዚአብሔር ልጅ እሰጥሃለሁ ብሎ የተስፋ ቃል የገባለት ከሣራ እንጂ በእቁባት መንገድ ከአጋር አልነበረም። ዳሩ ግን አብርሃም በእምነቱ ስለ ደከመና ተስፋም ስለ ቆረጠ የሚስቱን (የሣራን) ቃል በመስማት ወደ አጋር የመግባቱን እርምጃ ወሰደ። ነገር ግን የእግዚአብሔር ዓላማና የተስፋው ቃል ፍጻሜ አጋር ከወለደችው ልጅ (እስማኤል) ጋር ሳይሆን ሣራ ወደ ፊት ከምትወልደው ልጅ (ይስሐቅ) ጋር ስለሆነ እግዚአብሔር ወደ ሣራና አብርሃም መጥቶ የተስፋ ቃላቸውን እንደገና አደሰላቸው። ይስሐቅም የሚወለድበት የአንድ ዓመት ቀጠሮ ተሰጣቸው (ዘፍጥ. 18÷9-15)።

ከዚህ ውጪ እስማኤል ነቢይ፣ የእግዚአብሔር መልእክተኛና ቀጠሮ አክባሪነቱ መጽሐፍ ቅዱስ አይናገርም። ታዲያ መቀበል የሚገባን የቁርአንን ታሪክ ወይስ የመጽሐፍ ቅዱስን ነው?

## 2.6 አብርሃምና እስማኤል ካዕባን ስለ መገንባታቸው

*«ለኢብራሂምም የቤቱን (የካባን) ስፍራ መመለሻ ባደረግንለት ጊዜ በኔ ምንንም አታጋራ፤ ቤቴንም ለሚዞሩትና ለሚቆሙበት ለሚያጎነብሱትና በግምባራቸውም ለሚደፉት ንጹሕ አደርግላቸው፤ (ባልነው ጊዜ አስታውስ)»* (ቁርአን ሱረቱ 22:26)።

ሙስሊም ተንታኞች ይህን የቁርአን አንቀጽ በሚከተለው መንገድ ተንትነውታል:-

*«ኢብራሂም ከልጃቸው ጋር ከተገናኙ በኋላ በዚህ ቦታ ላይ አላህ የሚመለክበት ቤት እንዲሰሩ አዘዛቸው። ቤቱ የሚሠራበትንም ቦታ አመላከታቸው። እስማኤልም 'አባቴ ሆይ ፈጣሪህ ያዘዘህን ሁሉ ፈጽም። ለዚህ ክቡር ተግባር እኔ ከጎንህ በመቆም በአስፈላጊው ነገር ሁሉ አግዝሃለሁ' በማለት ደገፏቸው። እስማኤል ድንጋይ እያቀበሏቸው አባትና ልጅ ግንባታውን ለመቀጠል ተዘጋጁ፤ ኢብራሂም ለእስማኤል:- 'ለሰዎች ምልክት ይሆናቸው ዘንድ በማዕዘኑ ላይ የማስቀምጠው ጥሩ ድንጋይ መርጠህ አምጣልኝ' አሏቸው። መልአኩ ጂብሪል 'ጥቁሩን ድንጋይ'*

*እንዲያኖሩ ነገራቸው:: የግንባታውን ሥራ ሲያከናውኑ:- 'ጌታችን ሆይ! ከኛ ሥራችንን ተቀበል፤ አንተ በሚውና አዋቂው ነህና' በማለት ግንቡ እያደገ በሔደ ጊዜ ሽማግሌው እንደልባቸው ድንጋይ መሸከም ሲሳናቸው አንድ ድንጋይ ላይ ቆመው መሥራት ጀመሩ:: ይህም 'መቃሙ ኢብራሂም' ተብሎ ይጠራል»*[3]::

እንደ ቁርአን አገላለጽ እግዚአብሔር በመካ ካዕባን ለአብርሃም ቅዱስ የማምለኪያ ስፍራ እድርጎ ሰጥቶታል:: ይሁንና ግን፣ አብርሃም መካ ሄዶ እንደ ሚያውቅ የሚያሳዩ ምንጮች ወይም ታሪካዊ መረጃዎች በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በሌሎች የሉም:: ከዚህም በላይ አብርሃምና ልጁ እስማኤል ካዕባን እንዳነፁ ወይም እንደገነቡ የእስልምና ምንጮች ይገልጻሉ:: ሆኖም ከእስልምና በፊት ካዕባ በመካ የነበሩት የሳቢያኖች (ጣዖት አምላኪዎች) ቅዱስ ስፍራ እንደ ነበር ምንጮች ይጠቁማሉ::

እንግዲህ አብርሃምና እስማኤል የእስልምና ቅዱስ የማምለኪያ ስፍራ ካዕባን ስለ መገንባታቸው መጽሐፍ ቅዱስ አይናገርም:: ታዲያ አብርሃምና እስማኤል ካዕባን ገንብተዋል የሚለውን መጽሐፍ የቁርአንን ቃል ነው ማመን የሚገባን ወይስ ስለ ካዕባ ፈጽሞ የማይናገረውን የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ነው?

## 2.7 ሎጥ የሰዶም ሰዎች ሁለቱን ሴት ልጆቹን እንዲያገቡአቸው ስለ መጠየቁ

*«(ሉጥም):- እነኝህ ሴት ልጆቼ ናቸው፤ ሠሪዎች ብትኾኑ (አግቧቸው) አለ»* (ቁርአን ሱረቱ 15÷71)::

*መጽሐፍ ቅዱስ* ሎጥ በራሱ ምርጫ ከአብርሃም ተለይቶ በሰዶም ሰዎች መካከል መቀመጡን ይናገራል (ዘፍጥ. 13÷10):: የሰዶም ሰዎች እጅግ እስጸያፊ የሆነ የግብረ ሰዶም ኃጢአት ልምምድ በከፍተኛ ሁኔታ በመቀጠላቸው ምክንያት እግዚአብሔር ከምድረ ገጽ ሊደመስሳቸው ወስነ:: ነገር ግን ሎጥንና መላው ቤተሰቡን ሰማዳን ሁለት መላእክት ወደ ሎጥ ቤት በመጡ ጊዜ የሰዶም ሰዎች ተሰብስበው በመምጣት እንዲህ አሉት:- *«በዚህ ሌሊት ወደ ቤትህ የገቡት ሰዎች ወዴት ናቸው? እናውቃቸው ዘንድ ወደ እኛ አውጣቸው»* (ዘፍጥ. 19÷50) አሉት:: ሎጥም እንዲህ ሲል መለሰላቸው:- *«ወንድሞቼ ሆይ ይህን ክፉ ነገር አታድርጉ እነሆ ወንድን ያላወቁ ሁለት ሴቶች ልጆች አሉኝ፥ እነርሱን ላውጣላችሁ እንደ ወደዳችሁም አድርጓቸው፥ በእነዚህ ሰዎች ብቻ ምንም አታድርጉ፥ እነርሱ በጣሪያዬ ጥላ ሥር ገብተዋልና»* (ዘፍጥ. 19÷7-8) አላቸው::

ነገር ግን በቁርአን ላይ የተጻፈው *«አግቡአቸው»* የሚል ቃል ነው:: እዚህ ላይ መገንዘብ የሚኖርብን እንግዶቹን ፍለጋ ወደ ሎጥ ቤት የመጡት የአገሬው ሰዎች ከብላቴኖች እስከ ሽማግሌዎች መሆናቸው ነው:: ታዲያ ስንቶቹ ናቸው ሁለቱን የሎጥ ሴት ልጆች የሚያገቡአቸው? በመሠረቱ የሰዶም ሰዎች ፍላጎት የተቀደሰ

3. ገድለ ነቢያት በቁርአን ክፍል አንድ መጽሐፍ፤ ደራሲ ዓፊፍ ዓብዱልፈታህ ጠበራ፤ ትርጉም:- አወል ረታ ሀምሌ 1985 አዲስ አበባ ገጽ 141



ጋብቻ ሳይሆን ርኩሰት ነው:: ፆታ የማይመርጡ አእምሮአቸው የረከሰ፣ ግብረ ሰዶማውያን ናቸው:: ለዚህ ነው እግዚአብሔር ክፉኛ የተቆጣባቸው:: ሁለቱ መላእክት ሰዎች መስለዋቸው ነው እንደ ልማዳቸው ሊገናኙአቸው ወደ ሎጥ ቤት የተመሙት፤ እንዲያወጣላቸውም ሎጥን ጠየቁት:: ይህ ደግሞ ጥፋታቸውን የሚያፋጥን ምልክት ነበር:: የሰዶም ሰዎች ዕጣ ፋንታ በኃጢአታቸው ምክንያት መደምሰስ ነውና ፍርድ ተከናወነባቸው::

እንግዲህ ቁርአን *«አግቡአቸው»* ሲል፣ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ *«እነርሱን ላውጣላችሁ እንደ ወደዳችሁም አድርጓቸው»* ይላል:: ታዲያ እውነተኛው ታሪክ የቁርአን ወይስ የመጽሐፍ ቅዱስ ነው?

## 2.8 የሎጥ ሚስት የጨው ዓምድ ሆና እንደምትቀር መላእክት አስቀድመው ስለ መናገራቸው

*«በርሷ ውስጥ ሉጥ አልለ እኮ አሏቸው፤ እኛ በውስጧ ያለውን ይበልጥ ዐዋቂ ነን፤ (እርሱን) በእርግጥ እናድነዋለን፤ ቤተሰቦቹንም ጭምር፤ ሚስቱ ብቻ ስትቀር፤ እርሷ በጥፋቱ ውስጥ ከሚቀሩት ናት አሉት»* (ቁርአን ሱረቱ 29÷32-33)::

ሎጥ ከሰዶም እደጋ በእግዚአብሔር ዕርዳታ ነጻ እንደ ወጣ የሚናገረው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 19 ላይ የሚገኘው ታሪክ ነው:: እግዚአብሔር ኃጢአተኞችንና ዐመጸኞችን ሰመደምሰስ ወስኖ ሁለት መላእክት ወደ ሰዶም እንደ ላካቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል:: ሎጥና መላው ቤተሰቡ (ሚስቱ ጭምር) ከሰዶም በፍጥነት እንዲወጡ የእግዚአብሔር መላእክት አዘው ነበር:: በተሰጣቸው ትእዛዝ መሠረት ሎጥ፣ ሚስቱና ሁለት ሴት ልጆቻቸው ሰዶምን ሰቀው ጉዞ ጀመሩ (ዘፍጥ. 19÷15-16):: ከወጡ በኋላ ወደኋላ እንዳይመለከቱ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸው ነበር (ዘፍጥ 19÷17):: በመሆኑም እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ የሎጥ ሚስት የጨው እምድ ሆና መቅረት የቻለችው ማስጠንቀቂያውን በመጣስ ወደኋላ ዘወር ብላ ስለ ተመለከተች እንጂ፣ መላእክት አስቀድመው አልተናገሩም ነበር (ዘፍጥ 19÷26):: ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ሚናገረው ከሆነ ፈቃደኞች ቢሆኑ ኖሮ ከጥፋቱ አደጋ የመዳን ዕድል ለእማቾቹም ነበራቸው (ዘፍጥ 19÷12):: ስለሆነም የሎጥ ሚስት ከጥፋቱ ውስጥ ከሚቀሩት መሆንዋን የእግዚአብሔር ቅድመ ውሳኔ እንደ ነበረ መጽሐፍ ቅዱስ አይናገርም::

በመሠረቱ እንደ ቁርአን አገላለጽ:- *«ቤተሰቦቹንም ጭምር»* ከተባለ ስለ ምን የሎጥ ሚስት ከሚቀሩት ወይም ከሚጠፉት ጋር ትሆናለች? የሎጥ ሚስት የቤተሰቡ አካል አይደለችም እንዴ? እንግዲህ በዚህኛውም ነጥብ መጽሐፍ ቅዱስና ቁርአን ያቀረቡት የተለያየ ሐሳብ ከሆነ እውነተኛ ታሪክ የቁርአን ወይስ የመጽሐፍ ቅዱስ ነው?

# III. ሙሴ፣ አሮን፣ ፈርዖንና ሐማን በሚመለከት

## 3.1 ሙሴ አሮንን እንዲልከው ለእግዚአብሔር ስለ መናገሩ

*«ልቤም ይጠበባል! ምላሴም አይፈታም! ስለዚህ ወደ ሃሩን ላክ»* (ቁርአን ሱረቱ 26÷13፤ ሱረቱ 28÷34)።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሙሴ ሲናገር፣ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በወቅቱ ወዲያው ያልተቀበለበት ምክንያት እንደበተ ኮልታፋ ስለሆነ ብቃት የለኝም በማለት ነበር። ቁርአንም የሙሴ አንደበት ኮልታፋ እንደሆነ አልሸሸገም። በመሆኑም እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ አሮንን የመረጠውና የሙሴ ረዳት እንዲሆን ያደረገው ራሱ እግዚአብሔር እንጂ ሙሴ አሮንን አልመረጠውም ነበር (ዘጸአ. 4÷14-16)።

በአንጻሩ ደግሞ ቁርአን ሙሴ አሮንን መረጠ ይላል። መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ አሮን የሙሴ ረዳት እንዲሆን የመረጠውና የሾመው እግዚአብሔር ራሱ ነው ይላል። ታዲያ እውነተኛው ታሪክ የትኛው መጽሐፍ ያቀረበው ይሆን?

## 3.2 የፈርዖን አስማተኞች ገመዶች እንደጣሉ

*«ገመዶቻቸውንና በትሮቻቸውንም ጣሉ! በፈርዖንም ክብር ይኹንብን! እኛ በእርግጥ አሸናፊዎቹ እኛ ነን! አሉ»* (ቁርአን ሱረቱ 26÷44)።

ቁርአን የግብጽ አስማተኞች ገመዶቻቸውንና በትሮቻቸውንም ጭምር ቀላቅለው እንደጣሉ ይናገራል። ይህም ታሪክ እንደ ሌሎቹ ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አይገኝም። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው ከሆነ የግብጽ አስማተኞች ገመዶቻቸውን ሳይሆን የሙሴን በትር የሚመስል በትሮቻቸውን ነበር የጣሉት (ዘጸአ. 7÷12)። ሙሴ በትሩን መሬት ላይ በጣለ ጊዜ ወዲያው እባብ ሆነች። በተመሳሳይ ሁኔታ የግብጽ ጠንቋዮችም /አስማተኞችም/ በትሮቻቸውን በጣሉ ጊዜ እባብ ሰመሆን በቅተው ነበር። ነገር ግን የእግዚአብሔር ኃይል ከአስማተኞች ኃይል የላቀና ከፍ ያለ ስለሆነ የሙሴ በትር የአስማተኞችን ዋጠች። የዓለማት ጌታ እግዚአብሔር ታላቅና አሸናፊ ነው!

ስለሆነም ቁርአን የግብጽ አስማተኞች በትሮቻቸውንና ገመዶቻቸውን ቀላቅለው ጣሉ ሲል፣ በአንጻሩ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ገመዶቻቸውን ሳይሆን የሙሴ ዓይነት የሚመስል በትሮቻቸውን እንደጣሉ ይናገራል። ታዲያ እውነተኛው ማን ይሆን? ቁርአን ወይስ መጽሐፍ ቅዱስ ነው?

## 3.3 ሙሴ በትሩን ጥሉ እባብ በሆነች ጊዜ ሸሽቶ አለመመለሱ

*«በትርህንም ጣል (ተባለ፤ ጣለም)! እርሷ እንደ ትንሽ እባብ በፍጥነት ስትስለከለክ ባያትም ጊዜ፣ ፊቱን ዞሮ ሸሸ፤ አልተመለሰምም። ሙሳ ሆይ! አትፍራ! እኔ መልክተኞቹ እኔ ዘንድ አይፈሩምና»* (ቁርአን ሱረቱ 27÷10)።



እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ግብጽ ለመላክ በወሰነ ጊዜ ንጉሥ ፈርዖን እግዚአብሔር እንደ ላከው ያምን ዘንድ በምልክትና በተአምራት ጭምር ነበር። የሚጠበቀው ውጤትም የእስራኤል ልጆችን ከስደት በማውጣት እግዚአብሔር ወደ ሰጣቸው ርስታቸው ይገቡ ዘንድ ነው። ሙሴ ይህን መለኮታዊ ትእዛዝ ከእግዚአብሔር ተቀብሎ ነበር። የሙሴ ተልዕኮም ለዚህ ነው። ግባቸውም ቀይ ባሕርን ተሻግረው ከነዓን መግባት።

ነገር ግን በቁርአን ያለው ቃል አንጻራዊ ነው። ምክንያቱም ሙሴ በትሩን በጣለ ጊዜ እባብ ሆና መንቀሳቀስ በጀመረች ጊዜ፣ ፈርቶ ስለ ሸሸ ፈጽሞም እንዳልተመለሰ ቁርአን ይናገራል። ሽሽቱን በቀጠለ ጊዜ እግዚአብሔር ሙሴን ጠርቶ 'መልእክተኞች አይፈሩም አንተ ስለምን ፈርተህ ትሸሻለህ' በማለት እንደ ወቀሰው ቁርአን ተጨማሪ መግለጫ ይሰጣል። ሆኖም ሙሴ የእግዚአብሔርን ወቀሳ ሰምቶ መመለሱን ደግሞ ቁርአን አይናገርም። ይህም ደግሞ እንደ ሌሎቹ ታሪኮች ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አይገኝም። እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ግብጽ ሲልከው ማድረግ የሚገባውን የእርሱ ተልዕኮና ግብ ምን እንደሆነ አስቀድሞ ነግሮት ነበር። ተከምራትንም ቢሆን አስማምዶታል። ተአምራት የሚያደርግባትም በትር በእጁ ነበረች (ዘጸአ. 4÷17)። ሌላው መታወቅ ያለበት ሙሴ በትሩን በመጣል እባብ በሆነች ጊዜ ደንግጦ የሸሸው በመጀመሪያ በምድያም ሳለ እንጂ፣ በግብጽ በፈርዖን ፊት አለመሆኑ ነው (ዘጸአ. 4÷25)። ሙሴ ላለመታዘዝ ከእግዚአብሔር ጋር በተከራከረ ጊዜ ይታዘዝ ዘንድ እግዚአብሔር ምልክቶችን አሳይቶታል። ሙሴ በትሩን መሬት ላይ ጥሉ እባብ በሆነች ጊዜ ደንግጦ ማፈግፈጉ እውነት ነው። ለምን ቢባል? ሙሴ በሕይወት ዘመኑ ይህን ክስተት ከይቶ ስለ ማያውቅ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። ነገር ግን *«ፊቱን ዞሮ ሸሸ አልተመለሰምም»* የሚለው የቁርአን ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ጋር ይቃረናል እንጂ አይጣጣምም። *«አልተመለሰምም»* ማለት ሙሴ ለተላከበት ዓላማ ወደ ግብጽ አልሄደም እንደ ማለት ነው። ወይም ደግሞ ድርጊቱ በግብጽ በፈርዖን ፊት ሆኖ ከሆነ የእስራኤል ልጆች በሙሴ መሪነት ከግብጽ አልወጡም እንደ ማለት ነው።

*ታዲያ* ቁርአንና መጽሐፍ ቅዱስ የተለያየ ታሪክ ካቀረቡ እውነተኛ ታሪክ ነው ብለን መቀበል የሚገባን የየትኛውን መጽሐፍ ታሪክ ነው?

## 3.4 ፈርዖን ሐማ ግንብ እንዲያሠራለት ስለ መጠየቁ

*«ፈርዖንም፦ ሃማን ሆይ! መንገዶችን እደርስ ዘንድ ረዥም ሕንፃን ለኔ ካብልኝ የሰማያትን መንገዶች (እደርስ ዘንድ) ወደ ሙሳም አምላክ እመለከት ዘንድ»* (ቁርአን ሱረቱ 40÷37)።

*«ፈርዖንም እናንተ ጭፍሮች ሆይ! ከኔ ሌላ ለናንተ አምላክን ምንም አላወቅሁም፤ ሃማንም ሆይ! ጭቃን ለኔ አቃጥልልኝ፤ (ጡብ ሥራልኝ)! ለኔም ከፍተኛ ሕንጻን ስራልኝ፤ ወደ ሙሳ አምላክ ልወጣ እከጃላለሁና»* (ቁርአን ሱረቱ 28÷38)።

እንደ ቁርአን አገላለጽ ፈርዖን ወደ ሙሴ አምላክ ለመድረስ ባለው ምኞት ረጅም ሕንፃ እንዲያንጽለት የጠየቀው ሐማን ነው። ይሁንና ግን፣ ሐማ ማን ነው? ብለን እንጠይቃለን። ምክንያቱም ሐማ ከፈርዖን ጋር በተያያዘ በሌሎች የቁርአን አንቀጾች በአንድ አገርና በአንድ ዘመን እንደ ኖሩ ተደርገው ቀርበዋል። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በተለይም በኦሪት ዘጸአትም ሆነ በሌሎች የሙሴ መጻሕፍት ስለ ፈርዖን የሕንፃ ግንባታ ዕቅዶችም ሆነ ስለ ሐማ ምንም የተጠቀሰ ነገር እንደሌለ መረዳት ይቻላል።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሐማ የሚናገረው በፋርስ አገር በንጉሥ አርጤክስስ ዘመነ መንግሥት እንደ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆኖ ስላገለገለው ግለሰብ ብቻ ነው (አስቴ. 3÷1)። ታዲያ ቁርአን ፈርዖንና ሐማን እንዴት አድርጎ ነው አንድ ላይ አገናኝቶ የጠቀሳቸው? በአንድ ዘመን እንደነበሩ አድርጎ በቁርአን መጠቀሱስ እንዴት ሊከሰት ቻለ? ብለን በድጋሚ እንጠይቃለን።

በመሠረቱ የዚህ የሕንፃ ሥራ ወይም ግንባታ ጉዳይ በመጽሐፍ ቅዱስ በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 11 ላይ የሚገኘውን ታሪክ ያስታውሰናል። ግንቡንም የሠራው ግለሰብ ወይም ሐማ ሳይሆን በአንድ ቋንቋ የሚናገሩና የተባበረ አንድነት የነበራቸው ሕዝቦች ነበሩ። ዓላማቸውም በዓይነቱ ልዩ የሆነ ሰማይ ጠቀስ ሕንፃ ወይም ግንብ ሠርተው በምድር ላይ ሳይበተኑ በማቸውን በማስጠራት ዝናቸው ለዓለም ሁሉ እንዲታወቅ የማድረግ ፍላጎት ወይም ጥማት ነበር። በመሆኑም *«ጭቃ ለእኔ አቃጥልልኝ»* የሚለው የቁርአን ቃል፣ በመጽሐፍ ቅዱስ፦ *«ኑ ጡብ እንስራ በእሳትም እንተኩሰው»* ከሚለው ዐረፍተ ነገር ጋር ከሐማ በቀር ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ነው ማለት ይቻላል።

ታዲያ እንደ ሌሎቹ ታሪኮች ሁሉ በዚህም ርዕስ ጉዳይ ሁለቱ መጻሕፍት ያቀረቡት የተለያየ ከሆነ እውነተኛ ታሪክ የትኛው ይመስልዎታል? ከዚህም ሌላ ፈርዖንና ሐማ በአንድ ዘመንና በአንድ አገር ካልኖሩ ቁርአን እንዴት አንድ ላይ ሊጠቅሳቸው ቻለ?

## 3.5 ሙሴ ዮቶርን ለሚስት ብሎ ለስምንት ዓመት ስለ ማገልገሉ

*«ስምንት ዓመታት ልታገለግለኝ እኔ ከእነዚህ ሁለት ሴቶች ልጆቼ አንዲቱን ላጋባህ እሻለሁ፤ አሥርንም ብትሞላም ከአንተ ነው፤ ባንተ ማስቸገርንም አልሻም፣ አላህ የሻ እንደሆነ ከመልካሞቹ ሰዎች ኾኜ ታገኘኛለህ አለው»* (ቁርአን ሱራቱ 28÷27)።

ይህ የቁርአን አንቀጽ ሐሳብ ወይም ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ፈጽሞ የለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ሙሴ አማቹን ዮቶርን ለስምንት ዓመትና ለሚስት ብሎ እንዳላገለገለው መረዳት ይቻላል። ሆኖም የቁርአን ታሪክ ከላባና ከያዕቆብ ታሪክ ጋር አንድ ነው ባይባልም ተቀራራቢ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። ምክንያቱም ያዕቆብ ላባን ያገለገለው ራሔልና ሊያን ለማግባት ሲል አሥራ አራት ዓመት፣ ለበጎች ሲል ደግሞ ስድስት ዓመት፣ በጠቅላላው ያዕቆብ ላባን ያገለገለው ለሃያ ዓመት ነበር።



ስለሆነም ከመጽሐፍ ቅዱስ ማረጋገጥ እንደሚቻለው ዮቶር በባት ሴት ልጆች ነበሩት። ከሰባቱ ሴት ልጆች መካከል ሙሴ አንዷን (ሲፖራን) ወደዳት፤ እርሷም ወደደችው። አባቷ ዮቶርም ፈቃደኛ በመሆን ከሙሴ ጋር እንዲጋቡ ተስማማ (ዘጸአ. 2÷16-22)።

ስለሆነም የቁርአን እና የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የተለያየ መሆኑን እንረዳለን። *'ስምንት ዓመት ብታገለግለኝ እንዲቷን ልጄን አድርልሃለሁ፤ ሁለት ዓመት ጨምረህ አሥር ዓመት ብትሞላ'* ደግሞ የሚል ታሪክ የሚገኘው በቁርአን እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አይገኝም።

ልብ ይበሉ! የሙሴ ታሪክ የተጻፈው ከቁርአን በፊት ቢያንስ ከ1500 ዓመታት በላይ ነው። ታዲያ በእርስዎ አመለካከት ተአማኒነት ያለው ታሪክ የቁርአን ወይስ የመጽሐፍ ቅዱስ ነው?

## 3.6 ሙሴ ወደ ፈርዖን፣ ሐማና ቆሬ ስለ መላኩ

*«ሙሳንም በታምራቶቻችንና በግልፅ ማስረጃ በእርግጥ ላክነው፤ ወደ ፈርዖንና ወደ ሃማንም ወደ ቃሩንም (ላክነው)»* (ቁርአን ሱራቱ 40÷24)።

ሙሴ ለልዩ ዓላማና ተልዕኮ ወደ ግብጽ ንጉሥ ፈርዖን ዘንድ ስለ መላኩ መጽሐፍ ቅዱስ በሚገባ አብራርቶ ይናገራል። የተልዕኮው ዓላማና ግብም በስደት ለአራት መቶ ዓመታት ያህል የተገዙ፣ የተጨቆኑና የተሰቃዩትን የእስራኤልን ሕዝብ በመምራት ወደ ተስፋይቱ አገር እንዲገቡ ማድረግ ወይም ማስቻል እንደሆነ ይታወቃል። በመሆኑም ፈርዖን በዘመኑ የግብጽ ንጉሥ እንደ ነበረ የታወቀ ነው። ሙሴም የተላከው ወደ ፈርዖን ነው። አወዛጋቢው ነገር ሐማ በግብጽ ይኖር ነበር? በግብጽስ ሥልጣን ነበረው? ቆሬስ ሥልጣን ነበረው? የሚል ነው። *'ቃሩን'* የሚለው የቁርአን አጠራር ወይም ስያሜ ቆሬ እንደሆነ ይታወቃል። ታዲያ ሙሴ ወደ ሐማና ወደ ቆሬ ተልኮአል ወይ?

በኦሪት ዘጸአትም ሆነ በአጠቃላይ በሌሎች የሙሴ መጻሕፍት ላይ ስለ ሐማ የተነገረ እንዳች ታሪክ እንደሌለ ቀደም ሲል ማየታችን ይታወሳል። ስለ ሐማ የምናውቀው ከላይ ለመግለጽ እንደ ተሞከረው በአርጤክስስ ዘመነ መንግሥት እንደ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆኖ ስላገለገለው ባለ ሥልጣን ብቻ ነው (አስቴ. 1÷1፤ 3÷1-2)። ስለ ቆሬ ደግሞ የምናውቀው የእስራኤል ሕዝብ ከግብጽ ወጥተው በምድረ በዳ ሳሉ፣ ከዳታንና ከወንድሙ አቤሮን ጋር በመሆን ለአሮን ብቻ የተሰጠውን የክህነት አገልግሎት ለራሳቸው የተመኙትን ግለሰብ ነው። እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር አገልጋዮች ላይ በመነሳታቸው ምክንያት የእግዚአብሔርን ቅዱስ ፈቃድ ሲቃወሙ ተገኙና እግዚአብሔር ቀሰፋቸው።

እንግዲህ ቁርአን ሐማንና ቆሬን ከየት አምጥቶ ነው ከፈርዖን ጋር የመደባቸው? ወይም ያገናኛቸው? ታዲያ ሁለቱ መጻሕፍት ያቀረቡት ታሪክ የተለያየ ከሆነ የትኛው መጽሐፍ የተናገረውን ታሪክ ነው መቀበል የምንችለው?

## 3.7 ፈርዖን ሙሴን ለመግደል ስለ መዛቱ

*«ፈርዖንም፡- ተውኝ፤ ሙሳን ልገደል፤ ጌታውንም ይጥራ፤ ያድነው (እንደ ኾነ)፤ እኔ ሃይማኖታችሁን ሊለውጥ፤ ወይም በምድር ውስጥ ጥፋትን ሊያሰራጭ እፈራለሁና አለ»* (ቁርአን ሱረቱ 40÷26)።

ቁርአን ፈርዖን ሙሴን ለመግደል ዝቶበት እንደ ነበር ይናገራል፤ ምክንያቱንም ሲገለጽ፣ 'ጥፋትን በምድር ላይ ስለ ሚያሰራጭ እፈራለሁና' በማለት ፈርዖን ስጋቱን እንደ ገለጸ ቁርአን ተጨማሪ ገለጻ ይሰጣል። ይህም እንደ ሌሎቹ ታሪኮች ሁሉ ፈርዖን ሙሴን ለመግደል እንደ ዛተበት ምንም ዓይነት መረጃ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አይገኝም። ፈርዖን እስራኤልን አልለቅም ብሎ ልቡን እንዳደነደነ ተጽፎአል። ከዚህም ሌላ *'ሙሴ አባክህን ሕዝቡን ለምን ሥራ ታስፈታቸዋለህ?'* በማለት እንደ ተናገረው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ይገኛል። ከዚህ በቀር ፈርዖን ሙሴን የመግደል ዛቻም ሆነ ሙከራ ማድረጉ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የለም።

እንግዲህ ቁርአን ፈርዖን ሙሴን ለመግደል እንደዛተበት ሲገልጽ፣ በአንጻሩ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ ምንም አይናገርም። ታዲያ የትኛውን መጽሐፍ ነው እንደ እግዚአብሔር ቃል አድርገን መቀበል የሚገባን?

## 3.8 ሙሴ በግብጽ ዘጠኝ ተአምራት ብቻ ስለ ማድረጉ

*«ሙሳም ግልጽ የኾኑን ዘጠኝ ታምራቶች በእርግጥ ሰጠነው፤ በመጣቸውም ጊዜ የእስራኤልን ልጆች (ከፈርዖን እንዲለቀቁ) ጠይቅ (አልነው)፤ ፈርዖንም፡- ሙሳ ሆይ! እኔ የተደገመብህ መኾንህን በእርግጥ እጠረጥርሃለሁ አለው»* (ቁርአን ሱረቱ 17÷101፤ በተጨማሪም ቁርአን ሱረቱ 27÷12 ይመልከቱ።

ቁርአን ሙሴ በግብጽ ዘጠኝ ተአምራት ብቻ እንዳደረገ ከመናገር ውጪ የተአምራቶቹን ዓይነት አልዘረዘረም። በአንጻሩ መጽሐፍ ቅዱስ ከቁርአን በተቃራኒ ሙሴ በግብጽ አስር ተአምራት እንዳደረገ ይናገራል። ይህም የሆነው ፈርዖን ልቡን እልከኛ በማድረግ ሕዝቡን አልለቅም ብሎ የበለጠ ማስጨነቁን በቀጠለ ጊዜ ነው ሙሴ ተአምራቶቹን ያደረጋቸው። የተአምራቶቹም ዓይነት የሚከተሉት ናቸው። እነዚህም፡- የውሃ ወደ ደም መለወጥ፣ ጓጉንቸር፣ ቅማል፣ የዝንብ መንጋዎች፣ ቸነፈር፣ ሻህኝ የሚያወጣ ቁስል፣ ነጎድጓድና በረዶ፣ አንበጣዎች፣ ጨለማና የበኩር ልጅ ሞት ናቸው።

እንግዲህ ቁርአን ሙሴ በግብጽ ዘጠኝ ተአምራት ብቻ እንዳደረገ ሲናገር፣ በአንጻሩ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ሙሴ በግብጽ ያደረጋቸው የተአምራት



ብዛት አስር እንደሆኑ ይናገራል። ታዲያ ትክክለኛው ታሪክ አስር ወይስ ዘጠኝ ይሆን?

## 3.9 ሙሴ ኢያሱ እንዲያስተምረው ስለ መጠየቁ

*«ሙሳ ለርሱ፡- ከተማርከው ነገር ቀጥተኛን (ዕውቀት) ታስተምረኝ ዘንድ ልከተልህን? አለው»* (ቁርአን ሱረቱ 18÷66 )።

ኢያሱ የሙሴ አገልጋይ እንደ ነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ዘጸአ 24÷13፤ ኢያሱ 1÷1)፤ የሙሴ አገልጋይ መሆን የጀመረውም ከልጅነቱ ጀምሮ ነው (ዘኁል. 11÷28)። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ የእግዚአብሔርን ኃይል፣ ታላቅነቱንና ተአምራቱን በሙሴ እግር ሥር ተቀምጦ የተማረው ኢያሱ እንጂ፣ እንደ ቁርአን አገላለጽ ሙሴ ኢያሱን እንዲያስተምረው የጠየቀበት ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ የለም። ሙሴ እጆቹን በኢያሱ ላይ በመጫኑ ምክንያት ኢያሱ የጥበብ መንፈስ ተሞላ (ዘጸአ 34÷9)። ኢያሱ የተቀበለው ወይም የተሞላው የጥበብ መንፈስ ሙሴን ተከቶ ሕዝቡን የሚመራበት መለኮታዊ ጥበብ ነበር። በሙሴ ምትክ መሪ እንዲሆን እግዚአብሔር የመረጠበት ምክንያት በእምነቱ፣ በታማኝነቱና መንፈስ ቅዱስ ስለ ሞላበት ነው (ዘኁል. 27:18-20)።

ከዚህ ውጪ, ሙሴ ኢያሱ እንዲያስተምረው መጠየቁ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አይገኝም። ታዲያ መጽሐፍ ቅዱስና ቁርአን ያቀረቡት የተለያየ ታሪክ ከሆነ የትኛውን መጽሐፍ ነው መቀበል የሚገባን?

## 3.10 ሙሴ እግዚአብሔር በተገለጠለት ጊዜ ቤተሰቦቹን እዚህ ቆዩ ስለ ማለቱ

*«እሳትን ባየና ለቤተሰቦቹ፡- (እዚህ) ቆዩ፤ እኔ እሳትን አየሁ፤ ከርሷ ችቦን ላመጣላችሁ፤ ወይም እሳቲቱ ዘንድ መሪ ሳገኝ እከጅላለሁ ባለ ጊዜ (አስታውስ)»* (ቁርአን ሱረቱ 20÷10)።

እንደ ቁርአን አገላለጽ፡-

- ሙሴ እሳት ማየቱ፤
- ቤተሰቦቹን እዚህ ቆዩ ማለቱ፤
- ከእሳቱ ችቦን ላመጣላችሁ፤
- ከእሳቲቱ መሪ ሳገኝ እመኛለሁ ማለቱና የመሳሰሉት ናቸው።

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ ሙሴ በጎችን በመጠበቅ ላይ ሳለ ቁጥቋጦው በእሳት ሲነድ፣ ነገር ግን ቁጥቋጦው በእሳት ሳይቃጠል ተመለከተ (ዘጸአ. 3÷1-2)። እግዚአብሔር ከቁጥቋጦው መካከል ሆኖ ዕቅዱን በሙሴ አስታወቀ፤ ገለጸለት። በወቅቱ ከሙሴ ጋር የነበሩት በጎች እንጂ፣ ቤተሰቦቹ ወይም ሌሎች ሰዎች ከእርሱ ጋር አልነበሩም። ከቤተሰቡ ጋር የተገናኘው መለኮታዊውን ራእይ ካየና ከተቀበለ በኋላ እንጂ፣ እሳቱን በተመለከተበት ሰዓት ቤተሰቦቹ እዚያ ሰፍረ አልነበሩም። ነገር ግን ቁርአን ሙሴ እሳቱን ባየበት ጊዜ ቤተሰቦቹ እዚያው እርሱ ዘንድ እንደ ነበሩ

አድርጎ አቅርቦአል። ይህም ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ በእጅጉ ይለያል። ከዚህም ሌላ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ችቦም ሆነ ስለ ሌሎች ቁርአናዊ ነጥቦች አይናገርም።

እንግዲህ ቁርአን ከላይ ያለውን ታሪክ የሚያቀርብ ስሆንና መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ከቁርአን ለየት ባለ ሁኔታ የሚያቀርብ ከሆነ ተአማኒነት ያለው መጽሐፍ የትኛው ይመስልዎታል?

## 3.11 ሙሴ የፍየሎች እረኛ እንደነበር

*«ሙሳ ሆይ! ይህችም በቀኝ እጅህ ያለችው ምንድናት? (ተባለ)! ፦ እርሷ በትሬ ናት! በእርሷ ላይ እደገፍበታለሁ! በርሷም ለፍየሎች ቅጠልን አረግፍበታለሁ! ለኔም በርሷ ሌሎች ጉዳዮች አሉኝ አለ»* (ቁርአን ሱረቱ 20:17-18)።

ሙሴ በትር መያዙና በበትሩም ተአምራት ማድረጉን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ዘጸአ. 4÷2-5፤ 17÷9፤ 23÷14-16)። እግዚአብሔር በእጁ ምን እንዳለ ሙሴን መጠየቁ በኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ 4÷2 ላይ ተገልጾአል። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሙሴን በቀኝ እጅህ ያለችው ምንድናት? ብሎ አልጠየቀውም። ነገር ግን *'ይህች በእጅህ ያለችው ምንድናት?'* (ዘጸአ. 4÷2) የሚል ጥያቄ ብቻ ነበር።

በመሆኑም ቁርአን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሆነ ታሪክ ማቅረቡን መረዳት ይቻላል። በመሆኑም እነዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ የሌሉና በቁርአን ላይ ብቻ የሚገኙ ታሪኮች የሚከተሉት ነጥቦች ናቸው። እነዚህም፦

- ሙሴ በበትሩ እንደሚደገፍ፣
- ለፍየሎች ቅጠል እንደሚያረግፍበት፣
- ሌሎች ያልተጠቀሱ ጉዳዮችም ናቸው።

የሆነ ሆኖ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ሙሴ የፍየሎች እረኛ ሳይሆን የበጎች እረኛ ነበር (ዘጸአ. 3÷1)። ከዚህ ያለፈ ሙሴ በበትሩ እንደሚደገፍ፣ በበትሩም ለፍየሎች ቅጠል እንደሚያረግፍበትና ሌሎች ያልተጠቀሱ ጉዳዮች /ባይጠቀሱም/ እንደዚህ ዓይነት ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የለም። ታዲያ የትኛው መጽሐፍ ያቀረበውን ነው ማመን የሚገባን?

## 3.12 አሮንን ሙሴ ራሱ ስለ መምረጡ

*«ከቤተሰቦቼም ለኔ ረዳትን አድርግልኝ፤ ሃሩን ወንድሜን»* (ሱረቱ 20÷29-30)።

ስለ አሮን የሙሴ ረዳት መሆን ጉዳይ ቁርአን ሁለት የተለያዩ ሐሳቦችን አቅርቦአል። እነዚህም ቀደም ሲል ለማየት እንደ ሞከርነው *«ልቤም ይጠብባል፣ ምላሴም አይፈታም፣ ስለዚህ ወደ ሃሩን ላክ»* (ቁርአን ሱረቱ 26÷13) የሚል ሲሆን፣ በዚህኛው የቁርአን አንቀጽ ደግሞ ከላይ ማንበብ እንደ ቻልነው *«ከቤተሰቦቼ ለኔ ረዳት አድርግልኝ፣ ሃሩን ወንድሜን»* የሚል ነው።



ስለሆነም እነዚህ ሁለት የቁርአን አንቀጾችን አጽንኦት በመስጠት በምንመለከትበት ጊዜ እርስ በርስ እንደሚጋጩ መገንዘብ ይቻላል። ምክንያቱም የመጀመሪያው ሐሳብ ወደ 'ሃሩን ላክ' የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ 'ወንድሜ ሃሩንን ረዳቴ አድርግልኝ' ይላል። በመሆኑም እነዚህ ሐሳቦች ወይም ነጥቦች በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አይገኙም። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ ቀደም ሲል መጥቀስ እንደቻልነው አሮን የተመረጠው በሙሴ ምርጫና ፍላጎት ሳይሆን እራሱ እግዚአብሔር ነው አሮን የሙሴ ረዳት እንዲሆን የመረጠውና የሾመው። ታዲያ የትኛውን መጽሐፍ ነው አምነን መቀበል የሚገባን?

## 3.13 ፈርዖን አስማተኞችን በስቅላት ሊቀጣቸው ስለ መዛቱ

*«(ፈርዖንም) ለእናንተ ሳልፈቅድላችሁ በፊት ለርሱ አመናችሁን? እርሱ በእርግጥ ያ ድግምትን ያስተማራችሁ ትልቃችሁ ነው፣ እጆቻችሁንና እግሮቻችሁን በማናጋት (ግራና ቀኝ በማፈራረቅ) እቆራርጣችኋለሁ፣ በዘምባባም ግንዶች ላይ እሰቅላችኋለሁ፣ ማንኛችንም ቅጣቱ በጣም ብርቱ የሚቆይም መሆኑን ታውቃላችሁ አላቸው»* (ቁርአን ሱረቱ 20÷71)።

የፈርዖን አስማተኞች የእግዚአብሔር ኃይል ከእነርሱ አስማት እንደ ሚበልጥ በሚገባ ተረድተው እንደ ነበር መገመት ይቻላል። እንደ ቁርአን አገላለጽ አስማተኞቹ በአስማታቸው ምንም መፈየድ ሳሳልቻሉ ወይም ስላቃታቸው ፈርዖን እንደ ሚሰቅላቸው፣ እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን እንደ ሚቆራርጣቸው ይዝትባቸዋል። ይሁን እንጂ ኦሪት ዘጸአት ውስጥም ሆነ በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስለዚህ ርዕስ ጉዳይ የተጠቀሰ ነገር ምንም የለም። ከዚህም ባሻገር በጥንቷ ግብጽ ስቅላት፣ እጅና እግር መቁረጥ የሚባል ቅጣት እንዳልነበረ የታመኑ ምንጮች ይጠቁማሉ። ይህም ሆኖ ግን ቁርአን መሐመድንና እስልምናን ለሚቃወሙ ሰዎች ያዘዘው ቅጣትም ይህንኑ እንደ ነበር ቁርአን ይናገራል (ቁርአን ሱረቱ 5÷33)።

ታዲያ ይህ ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ከሌለ፣ ቁርአን ደግሞ በዚህ ዓይነት ሁኔታ የሚያቀርብ ከሆነ የትኛው መጽሐፍ የተናገረውን ነው አምነን መቀበል የሚገባን?

## 3.14 ሙሴ ድንጋዩን በመታው ጊዜ አሥራ ሁለት ምንጮች ስለ መፍለቃቸው

*«ሙሳንም ለሕዝቦቹ መጠጥን በፈለገ ጊዜ (የኾነውን አስታውስ)፣ ደንጊያውን በበትርህ ምታ አልነው፣ (መታውም) ከርሱም ዐሥራ ሁለት ምንጮች ፈለቁ፣ ሰዎቹ ሁሉ መጠጫቸውን በእርግጥ ዐወቁ፤ ከአላህም ሲሳይ ብሉ ጠጡም»* (ቁርአን ሱረቱ 2÷60)።

ሙሴ በበትሩ ድንጋዩን መትቶ ውኃ መፍለቁ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገር ቢሆንም፣ ነገር ግን የውኃውን ቁጥር ወይም ብዛት ግን ለይቶ አልገለጸም። ታዲያ የውኃውን ብዛት ለይቶ አሥራ ሁለት ምንጮ መፍለቃቸውን የተናገረውን ቁርአን፣ ወይስ በእግዚአብሔር ኃይል ብቻ ውኃ መፍለቁን

የተናገረውን መጽሐፍ ቅዱስን ነው እንደ እግዚአብሔር ቃል አድርገን እምነን መቀበል የሚገባን?

## 3.15. ሙሴ፣ አሮን፣ የወርቅ ጥጃውና አል - ሳምራዊው

«(አላህ) እኛም ከአንተ በኋላ፤ ሰዎችህን በእርግጥ ፈተነን፤ ሳምራዊውም አሳሳታቸው አለው። ... ቀጠሮህን በፈቃዳችን አልጣስንም፤ ግን እኛ ከሕዝቦቹ ጌጥ ሸክሞችን ተጫን (በእናንተ ላይ) ጣልናትም፤ ሳምራዊው እንደዚሁ ጣለ አሉት። ለነሱም አካል የኾነ ጥጃን ለርሱ መንጓር ያለውን አወጣላቸው፤ (ተከታዮቹ) ይህ አምላካችሁ የሙሳም አምላክ ነው፤ ግን ረሳው አሉትም» (ቁርአን ሱረቱ 20÷85-88)።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሙሴ፣ አሮንና የወርቅ ጥጃ በተመለከተ በቂ መረጃ ይሰጣል (ዘጸአ. 32÷1-35)። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ አሮን በሕዝቡ አስቸኳይ ጥያቄ ተገፋፍቶ በገዛ እጁ የወርቅ ጥጃ በመሥራት፦ «እስራኤል ሆይ እነዚህ ከግብጽ ምድር ያወጡህ አማልክትህ ናቸው» (ዘጸአ. 32÷4) እንዳለ ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እናነባለን። ነገር ግን ቁርአን ሕዝቡን ወደ ጥፋት የመራውም ሆነ ያሳሳታቸው አሮን አይደለም ይላል። ከዚህም ሌላ ቁርአን የወርቅ ጥጃውን የሠራው ሳምራዊ ነው ይላል። ሙሴ አል - ሳምራዊውን በሚገሥጽበት ጊዜ የጣዖቱ አመድ በባሕር ላይ እንደሚበተን ቁርአን በተጨማሪ ይናገራል (ቁርአን ሱረቱ 20፡97)።

ስመሆኑ በዘጸአት ውስጥ አንድም ጊዜ ያልተጠቀሰው ይህ ሳምራዊ ማን ነው? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ሰማርያና የወርቅ ጥጃ ጉዳይ ማየት እንችላለን። ይህም ከንጉሥ ሰሎሞን በኋላ በልጁ በሮብዓም የአገዛዝ ቀንበርና ብልሹ ምግባር ምክንያት የእስራኤል መንግሥት ለሁለት ተከፈለ። በዚህም ምክንያት ሰማርያ የሰሜኑ መንግሥት ርዕሰ ከተማ ሆነች። ሰማርያ የተመሰረተችው ሙሴና አሮን ካለፉ ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። የሰሜኑ መንግሥት የመጀመሪያው ንጉሥ ኢዮርብዓም የሚባል ሰው ነበር። «ንጉሡም ተማከረ እርሱም ሁለት የወርቅ ጥጆችን አድርጎ፦ እስራኤል ሆይ ወደ ኢየሩሳሌም ትወጡ ዘንድ ይበዛባችኋል ከግብጽ ምድር ያወጡህን አማልክቶችህን እይ አላቸው» (1ነገሥ. 12÷25-31) የሚል እናነባለን። ይህም አሮን ከአያሌ ምዕተ ዓመታት በፊት ከተናገረው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው። በመሆኑም ታዲያ ቁርአንና መጽሐፍ ቅዱስ ያቀረቡት የተሰያየ ታሪክ ከሆነ መቀበል የሚገባን የትኛውን መጽሐፍ ነው?



# VI. ያዕቆብና ልጆቹን በሚመለከት

## 4.1 ያዕቆብ ልጁ ዮሴፍ ሕልሞቹን ለወንድሞቹ እንዳይናገር ስለ ማስጠንቀቁ

«(አባቱም) አለ፦ ልጄ ሆይ! ሕልምህን ለወንድሞችህ አታውራ፤ ላንተ ተንኮልን ይሰሩብሃልና፤ ሰይጣን ለሰው ግልጽ ጠላት ነውና» (ቁርአን ሱረቱ 12÷5)።

ስለ ዮሴፍ ሕልሞች በመጽሐፍ ቅዱስ የምናገኘው በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 37 ላይ ነው። ዮሴፍ ሕልም አለመ፤ ለወንድሞቹም ነገራቸው' (ዘፍጥ. 37÷5)። ዮሴፍ ሌላ ተጨማሪ 'ሕልም ደግሞ አለመ፤ እንደገናም ለወንድሞቹ ነገራቸው' (ዘፍጥ. 37÷9) የሚል እናገኛለን። ዮሴፍ ሕልሞቹን ለወንድሞቹ ሲነግራቸው እጅግ በጣም እንደ ቀነበትና እንደ ጠሉት መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ከዚህ ውጪ ያዕቆብ ልጁ ዮሴፍ ሕልሞቹን ለወንድሞቹ እንዳያወራ ወይም እናዳይናገር ያስጠነቀቀበት አጋጣሚ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አይገኝም።

ታዲያ መቀበል የሚገባን የቁርአንን ወይስ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ ነው?

## 4.2 ስለ ዮሴፍና የጲጥፋራ ሚስት

«ጎሚታቸውንም በሰማች ጊዜ ወደነሱ ላከችባቸው፤ ምግብንም ለነርሱ አዘጋጀችላቸው፤ ከነሱም ለእያንዳንዳቸው ቢላዋን ሰጠች፤ በነሱም ላይ ውጣ አለችው፤ ባዩትም ጊዜ አደነቁት፤ እጆቻቸውንም ቆረጡ፤ አላህም ጥራት ይገባው፤ ይህ ሰው አይደለም፤ የማረ መልአክ እንጂ ሌላ አይደለም አሉ» (ቁርአን ሱረቱ 12÷31)።

የጲጥፋራ ሚስት ዮሴፍን ስመማረክ እንደሞከረች መጽሐፍ ቅዱስ መግለጹ እውነት ነው። ታሪኩም የሚገኘው በኦሪት ዘፍጥረት 39፡1-20 ላይ ነው። ይሁንና ግን ቁርአን ያቀረበውን ዝርዝር ሁኔታ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተጠቅሶ አናገኝም። ታዲያ ቁርአን ያቀረበውን ታሪክ ነው መቀበል የሚገባን ወይስ መጽሐፍ ቅዱስ ያቀረበውን ነው?

## 4.3 የዮሴፍ ወንድሞች አባታቸው ዮሴፍን ወደ እነርሱ እንዲልክ ስለ መጠየቃቸው

«ነገ ከእኛ ጋር ላከውና ይደሰት፤ ይጫወትም፤ እኛም ለእርሱ ጠባቂዎቹ ነን። ፦ እኔ እርሱን (ዮሱፍን) ይዛችሁ መኼዳችሁ በእርግጥ ያሳዝነኛል፤ እናንተም ከርሱ ዘንጊዎች ስትኾኑ ተኩላ ይበላዋል ብዬ እፈራለሁ አላቸው» (ቁርአን ሱረቱ 12÷12-13)።

በመጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ ታሪኩ የሚገኘው በኦሪት ዘፍጥረት 37÷12-36 ላይ ነው። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ መሠረት ከሆነ አሥሩ የያዕቆብ ልጆች በሴኬም የአባታቸውን በጎች እስማርተው ይጠብቁ ነበር። አባታቸው ያዕቆብም ወደ ሴኬም

ወርዶ የወንድሞቹን ደህንነት እንዲጠይቃቸውና እንዲጐበኛቸውም ዮሴፍን ላከው። ወንድሞቹም ዮሴፍ እነርሱ ወዳሉበት መምጣቱን በሩቅ አዩት። ከዚያም 'ያ ባለ ሕልም መጣ' ብለው ይገድሉት ዘንድ ተማካሩ። ከገደልነው በኋላ ለአባታችን ክፉ አውሬ በላው አንለዋለን በማለት አጥብቀው ተወያዩ። ነገር ግን ታላቅ ወንድማቸው ሮቤል ከምንገድለው ይልቅ ጉድጓድ ውስጥ ብንጥለው ይሻላል የሚል ሐሳብ አቀረበና ተቀባይነት አገኘ። ከዚያም ዮሴፍን ጉድጓድ ውስጥ ጣሉት። እንደገና በይሁዳ ሐሳብ አቅራቢነት ከጉድጓድ አውጥተው ለእስማኤላውያን ነጋዴዎች በሃያ ብር ሸጡት። እስማኤላውያን ነጋዴዎች ደግሞ ዮሴፍን አሳልፈው ግብጽ አገር ለሚገኘው ጲጥፋራ ለሚባል ባለሥልጣን ሸጡት።

ከዚያም ወንድሞቹ ፍየል አርደው የዮሴፍን ልብስ በደም ነከሩት። ወስደው ለአባታቸው አውሬ እንደ በላው አስመስለው ለምልክት አሳዩት። በዚህ ዓይነት ሁኔታ አባታቸውን አታለሉት። ያዕቆብ በደም የተጨማለቀውን የዮሴፍን ልብስ ባየ ጊዜ አውሬ እንደበላው አረጋገጠ፤ ክልቡም አዘነ። መጽሐፍ ቅዱስ የታሪኩን ቅደም ተከተል በዚህ ዓይነት ሁኔታ ያቀርባል። በአንጻሩ ግን ቁርአን  ደግሞ ያቀረበው በሚከተለው ዓይነት መንገድ ነው፡-

- ነገ ወደ እኛ ላከው (ወንድሞቹ)፤
- ይደሰት፤
- ይጫወት፤
- እኛ የእርሱ ጠባቂዎች ነን፤ ሲሉት አባታቸው ያዕቆብ ደግሞ መልሶ፡-
- እርሱን ይዛችሁ መሄዳችሁ ያሳዝነኛል፤
- እናንተ (አሥር ወንድሞቹ) ዘንጊዎች ናችሁ፤
- ተኩላም ይበላዋል፤
- እፈራለሁ የሚል ስጋት ነበር በቁርአን የተጻፈው።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ለማየት እንደ ሞከርነው የዮሴፍ ወንድሞች አይጀለም ወደ እነርሱ እንዲልክ አባታቸው ያዕቆብን የጠየቁት። ቁርአን ግን ወንድሞቹ አባታቸውን እንደጠየቁ አድርጎ አቅርቦአል። ከዚህም ሌላ ቁርአን የዘረዘራቸው ሌሎች ነጥቦች በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አይገኙም።

ታዲያ በዚህም ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስና በቁርአን መካከል ከፍተኛ ልዩነት ካለ የማንን ነው መቀበል የሚገባን?



# V. ንጉሥ ሰለሞንን በሚመለከት

## 5.1 ከሰይጣናት መካከል የንጉሥ ሰለሞን አገልጋዮች እንደሆኑ

*«ከሰይጣናትም ለርሱ (ሉልን ለማውጣት) የሚጠልቁንና ከዚያም ሌላ ያለን ሥራ የሚሰሩ (ገራዥለት)፤ ለነሱም ተጠባባቂዎች ነበርን»* (ቁርአን ሱረቱ 21÷13)።

በመጽሐፍ ቅዱስ የንጉሥ ሰለሞን ጥበብ በሰፊው ተዘርዝሮ ይገኛል (1ነገሥ. 3÷10-13)። ሆኖም ከሰይጣናት መካከል የንጉሥ ሰለሞን አገልጋዮች እንደ ነበሩ የሚገልጽ አንዳችም ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የለም። መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣን መንፈስ እንደሆነ ይናገራል። ቁርአን ደግሞ ለሰለሞን *'ገራዥለት'* የሚል ቃል ይጠቀማል። መንፈስ የሆነውን ሰይጣን እንደ ዱር እንስሳት አድርጎ ማቅረቡ አስገራሚ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ቁርአን ስለ ሰይጣን ሲናገር ግልፅ ጠላት እንደሆነ የሚከተሉት የቁርአን አንቀጾች ያረጋግጣሉ (ቁርአን ሱረቱ 2÷168,208፤ 6÷142፤ 7÷22፤ 35÷6፤ 17÷53፤ 36÷60)።

ታዲያ ሰይጣን ግልፅ ጠላት ከሆነ እንዴት የሰውን ልጅ ሊያገለግል ይችላል? በመሠረቱ እንዲህ ዓይነት ታሪክ ማመንና መቀበል የሚያስቸግር ነው። በመሆኑም ለግንዛቤ ይረዳን ዘንድ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱ የሰይጣን ባሕርያት የሚከተሉት ናቸው። እነዚህም፡-

- የወንድሞች ከሳሽ (ራእ. 12÷10)፤
- ባለጋራ (1 ጴጥ. 5÷8)፤
- የዓለም ሁሉ አሳች (ራዕ. 12÷9)፤
- ክፉው (ማቴ. 13÷19)፤
- ነፍሰ ገዳይ (ዮሐ. 8÷44)፤
- የሐሰት አባት (ዮሐ. 8÷44)፤
- ፈታኝ (1 ተሰ. 3÷5) . . . እነዚህና ሌሎችም ናቸው።

ታዲያ እነዚህን ባሕርያት የያዘው ሰይጣን ንጉሥ ሰሞንን እንዳገለገለ ተደርጎ መቅረቡ እንዴት ይታያል? ከክፉ ምን መልካም ነገር ይገኛል? ሰይጣን መልካም ተግባር ወይም የአገልጋይነት ተልዕኮ ሳይሆን የዓለም ሁሉ አሳች፤ ነፍሰ ገዳይ፤ የሐሰት አባትና አጥፊ መሆኑን ከባሕርይው አንጻር መረዳት ይቻላል።

## 5.2 ንጉሥ ሰለሞን ከወፎች ጋር የመነጋገር ችሎታ ነበረው

*«ሱለማይንም ዳውድን ወረሰ፤ አለም፡- ሰዎች ሆይ የበራርን ንግግር (የወፍን ቋንቋ) ተስተማርን፤ ከነገሩም ሁሉ ተሰጠን፤ ይህ እርሱ በእርግጥ ግልፅ የኾነ ችሮታ ነው»* (ቁርአን ሱረቱ 27÷16)።

የንጉሥ ሰለሞን ጥበብ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በሰፊው ስለ መገለጹ ቀደም ሲል ማየታችን ይታወሳል። ነገር ግን ንጉሥ ሰለሞን የወፍ ቋንቋ ስለ መማሩና ወፎች እርስ በርሳቸው ሲነጋገሩ የመስማት ችሎታ ነበረው የሚለው የቁርአን ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አይገኝም።

## 5.3 የንጉሥ ሰለሞን ሠራዊት ጋኔኖችና ወፎች ነበሩ

*«ለሱለይማንም ሰራዊቶች ከጋኔን ከሰውም ከበራሪም የኾኑት ተሰበሰቡ»* (ቁርአን ሱረቱ 27÷17)።

እንደ ቁርአን አገላለጽ የንጉሥ ሰለሞን ሠራዊት ወይም የጦር ኃይል የተገነባውና የተደራጀው በጋኔኖችና በወፎች እንዲሁም በሰዎች ነው። ይህም እንደ ሌሎች ታሪኮች ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የለም።

## 5.4 ጉንዳኖች እርስ በርስ ሲነጋገሩ ንጉሥ ሰለሞን ይሰማቸው ነበር

*«በጉንዳን ሸለቆ በመጡ ጊዜ አንዲት ጉንዳን፦ አላንተ ጉንዳኖች ሆይ! ወደ መኖሪያዎቻችሁ ግቡ፤ ሱለይማንና ሰራዊቱ እነርሱ የማያውቁ ሲኾኑ አይሰባብሩዋችሁ አለች። ከንግግርዋም እየሳቀ ፈርቱን ፈገግ አደረገ፤ ጌታዬ ሆይ! ያቺን በኔና በወላጆቼ ላይ የለገስካትን ጸጋህን እንዳመሰግን የምትወደውን በጎ ሥራ እንድሠራ ምራኝ፤ በችሮታህም በመልካሞቹ ባሮችህ ውስጥ አግባኝ አለ»* (ቁርአን ሱረቱ 27÷18-19)።

ቁርአን ንጉሥ ሰለሞን ጉንዳኖች ሲነጋገሩ ሰምቶ እንደተደነቀ ይናገራል። በእንጸሩ ምንም እንኳን የንጉሥ ሰለሞንን ጥበብ በመጽሐፍ ቅዱስ በሰፊው የተገለጸ ቢሆንም ሰለሞን ጉንዳኖች ሲነጋገሩ ይሰማቸው ነበር የሚለው ነጥብ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አይገኝም።

## 5.5 ሁድ ሁድ የተባለ ወፍ ለንጉሥ ሰለሞን ምስጢር ስለ መናገሩ

*«በራሪዎችንም ተመለከተ፤ አለም፦ ሁድ ሁድን ለምን አላየውም! በውነቱ ከራቁት ነበርን? ብርቱን ቅጣት በእርግጥ እቀጣዋለሁ፤ ወይም በእርግጥ ዐርደዋለሁ፤ ወይም ግልጽ በኾነ አስረጅ ይመጣልኛል (አለ)። (ወፉም) ዕሩቅ ያልኾነን ጊዜ ቆዩ፤ አለም፦ ያላወከውን ነገር አወቅኩ፤ ከሰበእም እርግጠኛ ወሬ አመጣሁልህ»* (ቁርአን ሱረቱ 27÷20-26)።

ይህ የቁርአን አንቀጽ ሁድ ሁድ የተባለው ወፍ (የዝናብ ወፍ) ለንጉሥ ሰለሞን ምስጢር መናገሩን የሚናገር ክፍል ነው። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሁድ ሁድ ስለ ተባለው ወፍና ምስጢር ስለ መናገሩ ጉዳይ ምንም የተጠቀሰ ነገር የለም።



## 5.6 ሁድ ሁድ ለሳባ ንግሥት መልዕክት ስለ ማድረሱ

*«(ሱለይማንም) አለ፦ እውነት እንደ ተናገርክ ወይም ከውሸታሞቹ እንደ ሆንክ ወደ ፊት እናያለን፤ ይህንን ደብዳቤዬን ይዘህ ኺድ፤ ወደ ነርሱም ጣለው፤ ከዚያም ከነሱ ዘወር በል፤ ምን እንደሚመልሱም ተመልከት። (እርሷም በደረሳት ጊዜ) አለች፦ አላንተ መማክርቶች ሆይ! እኔ ክብር ያለው ጽሑፍ ወደኔ ተጣለ፤ እርሱ ከሱለይማን ነው፤ እርሱም በአላህ ስም አጅግ በጣም ርኅሩህ በጣም አዛኝ በኾነው»* (ቁርአን ሱረቱ 27÷27-37)፤

እንግዲህ እነዚህ ቁርአን ያቀረባቸው ዝርዝር ሁኔታዎች በሙሉ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚታወቁ ታሪኮች አይደሉም። በመሠረቱ እነዚህ ነጥቦች ከሃይማኖታዊ አስተሳሰብ በላይ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል። ለምን ቢባል? ከወፎች ጋር መነጋገር መቻልና ጉንዳኖች እርስ በርስ ሲነጋገሩ መስማት፣ እንዲሁም ከሰይጣናት መካከል የንጉሥ ሰለሞን አገልጋዮች እንደነበሩ፣ የንጉሥ ሰለሞን ሠራዊት የተገነባውና የተደራጀው በጋኔኖችና በወፎች ነው የሚለው ቁርአናዊ ሐሳብ ከሰብአዊ አእምሮና ግምት በላይ ነው ቢባል እንደ ማጋነን አይሆንም። በመሆኑም በዘመናት መካከልና በታሪክ ውስጥ እንዲህ ዓይነት አስገራሚ ተአምራት ተደርገዋልን? ብለን ብንጠይቅ ስህተት አይሆንም።

ይሁንና ግን ወፎችና ጉንዳኖች የሚነጋገሩበት፣ በአየር ላይ የሚበር ዙፋንና ባሕር የሚመስል የመስተዋት ቤተ መንግሥት ያስበት መግለጫ የተገኘው፦ *«II Targum of the Book of Esther»* በተባለው የአይሁዶች አፈ ታሪክ ውስጥ ተጠቅሶ እንደሚገኝ ምንጮች ይጠቁማሉ።

ታዲያ እነዚህ ታሪኮች በመጽሐፍ ቅዱስ ሳይኖሩና ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ በሆነ በአይሁድ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ ከሆነና ቁርአንም ይህንኑ መልሶ እንደ አዲስ መገለጥ የሚተርክ ከሆነ እኛ መቀበል የሚገባን የትኛውን መጽሐፍ ነው?

# VI. ኢየሱስ ክርስቶስን በሚመለከት

ኢየሱስ ክርስቶስን በሚመለከት ቁርአን ያቀረባቸው በርካታ ታሪኮች አሉ:: ሆኖም ቁርአን ያቀረባቸው ነጥቦች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ይቃረናሉ እንጂ አይስማሙም፤ አይጣጣሙም:: በቁርአን ብቻ የሚገኙና በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያልተጠቀሱ ኢየሱስን የሚመለከቱ ከበርካታ ነጥቦች መካከል የተወሰኑትን ብቻ መርጠን ለማየት እንሞክራለን:: እነዚህም:-

## 6.1 በዘምባባ ዛፍ ሥር ስለ መወለዱ

*«ምጡ ወደ ዘምባባይቱ ግንድ አስጠጋት ዋ ምኞቴ! ምነው ከዚህ በፊት በሞትኩ፤ ተረስቼ የቀረሁ በሆንኩ፤ አለች»* (ቁርአን ሱረቱ 9÷23)::

ቁርአን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደው በዘምባባ ዛፍ ሥር ነው ይላል:: በተጨማሪም ቅድስት ማርያም ምጡ ስከፍተኛ ሁኔታ ስለ በረታባት ተማርራ ሞት እንደ ተመኘች ቁርአን ይናገራል::

በመጽሐፍ ቅዱስ እና በቁርአን ስለ ኢየሱስ አወላለድ ሰፊ ልዩነት አለ:: እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ ዘመኑ የሕዝብ ቆጠራ የሚካሄድበት ጊዜ ስለ ነበር ማርያምና ዮሴፍ ከትውልድ መንደራቸው ከገሊላ ናዝሬት ተነሥተው ለመመዝገብ ወደ ቤተልሔም ሄዱ:: በዚህን ጊዜ ማርያም የመውለጃዋ ጊዜ ደርሶ ስለነበር ምጥ ጀመራት:: ልጇ ኢየሱስንም ያለምንም ችግር ወለደች:: ማደሪያ ሥፍራ ሊያገኙ ስላልቻሉ አዳራቸውም በከብቶች በረት ውስጥ ሆነ (ሉቃ. 2÷1-7):: ከዚህ ውጪ ማርያም ሞት እንደ ተመኘችና በዘምባባም ዛፍ ሥር ኢየሱስን እንደ ወለደች መጽሐፍ ቅዱስ አይናገርም::

እንግዲህ ቁርአን ኢየሱስ በዘምባባ ዛፍ ሥር እንደ ተወለደ ሲናገር፣ በአንጻሩ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ኢየሱስ የተወለደው በዘምባባ ዛፍ ሥር እንዳልሆነ ይናገራል:: ታዲያ መቀበል የሚገባን የቁርአንን ታሪክ ወይስ የመጽሐፍ ቅዱስን ነው?

## 6.2 በሕፃንነቱ እንደ ትልቅ ሰው ስለ መናገሩ

*«በሕፃንነቱና በከፈኒሳነቱ ሰዎችን ያነጋግራል፤ ከመልካሞቹም ነው (ሐላት)»* (ቁርአን ሱረቱ 3÷46)::

*«ወደርሱም ጠቀሰች፤ በአንቀልባ ያለን ሕፃን እንዴት እናናግራለን አሉ:: (ሕፃኑም) አለ:- እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ፤ መጽሐፍን ሰጥቶኛል ነቢይም አድርጎኛል»* (ቁርአን ሱረቱ 19÷29-30)::

ቁርአን የኢየሱስን ተአምራት ያቀረበው በሕፃንነቱ ማለትም በእናቱ ጀርባ በአንቀልባ ሳለ ልክ እንደ ለላሳ ዓመት ወጣት ወይም እንደ አርባ ዓመት ጎልማሳ መናገር መቻሉ ነው:: ሆኖም እንዲህ ዓይነት ተአምር በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አይገኝም::



ኢየሱስ እንደ ማንኛውም ሰው እንደ ተወለደ እስልምና ያስተምራል:: ሲያስኘው ደግሞ ኢየሱስ ሕፃን ሳለ እንደ ትልቅ ሰው መናገር ችሎአል በማለት ቁርአን አቅርቦአል:: ይህ ሐሳብ ደግሞ ከእስልምና አስተምህሮ ጋር እንደሚጋጭ ማሰብ ይቻላል:: ምክንያቱም በተፈጥሮ ሕግ አንድ ሕፃን እንደ ትልቅ ሰው የተናገረበት የታሪክ አጋጣሚ አልነበረም::

ይሁንና ግን አዲስ የተወለደው ልጅ (ኢየሱስ) በሕፃንነቱ መናገር እንደሚችል የሚያትተው *«የሕፃንነት ወንጌል»* /The Gospel of Infancy/ በተባለው አዋልዳዊ የዓረብ መጽሐፍ ውስጥ ታሪኩ ተጠቅሶ እንደሚገኝ አስተማማኝ ምንጮች ይጠቁማሉ:: ታዲያ ታሪኩ እንዴት እንደ አዲስ መገለጥ ተደርጎ በቀጥታ በቁርአን ሊጻፍ ቻለ? እኛስ ማመንና መቀበል የሚገባን ቀደም ሲል ከነበረው አዋልዳዊ መጽሐፍ የተወሰደውን ታሪክ ወይስ አስተማማኝ ሆኖ ለዘመናት የኖረውን መጽሐፍ ቅዱስ ነው?

## 6.3 ከጭቃ ወፍ መፍጠር ስለ መቻሉ

*«እኔ ከጌታዬ ዘንድ በታምር መጣኋችሁ:: እኔ ለናንተ ከጭቃ እንደ ወፍ ቅርፅ እፈጥራለሁ፤ በርሱም እተነፍሳለሁ፤ በአላህም ፈቃድ ወፍ ይሆናል»* (ቁርአን ሱረቱ 3÷49)::

ቁርአን ኢየሱስ ተአምራት እንዳደረገ ቢያምንም በእግዚአብሔር ኃይል፣ ፈቃድና ዕርዳታ ብቻ እንዳከናወናቸው ብቻ ያስተምራል:: ስለሆኑም ቁርአን እግዚአብሔር አዳምን በፈጠረበት ዓይነት ኢየሱስ ከአፈር ወፍ እንዳበጀ ወይም እንደ ፈጠረ ይናገራል:: ይሁንና ግን ይህ ታሪክ የሚገኘው *«የእስራኤላዊው ቶማስ ወንጌል»* በሚል ርዕስ በተጻፈው የአዋልድ መጽሐፍ ውስጥ መሆኑ ተረጋግጦአል:: ሆኖም ምንም እንኳን ቁርአን የኢየሱስን ፈጣሪ መሆን የማያምን ቢሆንም ኢየሱስ የወፍ ቅርፅ ያለውን ፍጡር መፍጠሩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረትና ድጋፍ የለውም:: እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ መላው ፍጥረታት የተፈጠሩት በእርሱና ለእርሱ ነው (ዮሐ. 1÷3፤ ቈላ. 1÷15-18)::

ስለሆነም እኛ መቀበል የሚገባን ከአዋልድ መጽሐፍ በቀጥታ ተወስዶ የተጻፈውን የቁርአን ታሪክ ወይስ ከቁርአን በፊት ለረጅም ዓመታት ሕልውናውን ጠብቆ የኖረውን መጽሐፍ ቅዱስን ነው?

## 6.4 ሰዎች በቤታቸው የሚመገቡትን ስለ ማወቁ

*«... የምትበሉትንና በቤታችሁ የምታደልቡትን ሁሉ እነግራችኋለሁ፤ የምታምኑ እንደሆናችሁ ለእናንተ በዚህ ውስጥ በእርግጥ ታምር አለበት»* (ቁርአን ሱረቱ 3÷49)::

ይኸኛው የቁርአን አንቀጽ ደግሞ ኢየሱስ ሰዎች እቤታቸው ሆነው የሚመገቡትን ሁሉ ማወቅ መቻሉን የሚናገር ክፍል ነው:: እንዲህ ዓይነት የኢየሱስ ተአምር ተብሎ ለቁርአን የቀረበውና እውቅና የተሰጠው ታሪክ የመጽሐፍ ቅዱስ ድጋፍ የለውም:: ታዲያ እኛ መቀበል የሚገባን ቁርአን ያቀረበውንና

በመጽሐፍ ቅዱስ የሌለውን ታሪክ ወይስ መጽሐፍ ቅዱስ ያቀረበውን የኢየሱስ ተአምራት ብቻ ነው?

## 6.5 አለመሰቀሉና አለመሞቱ

*«እኛ የአላህን መልክተኛ የመርየምን ልጅ አልመሲሕ ዒሳን ገደልን በማለታቸውም (ረገምናቸው)፤ አልገደሉትም፤ አልሰቀሉትም፤ ግን ለነሱ የተገደለው ሰው በዒሳተመሰለ፤ ...»* (ቁርአን ሱረቱ 4÷157-158)::

ቁርአን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈጽሞ አልተሰቀለም፤ አልሞተም አያሰ ጠንካራ አቋሙን ያቀርባል:: አንደ ቁርአን አገላለጽ የተሰቀለው ኢየሱስ ራሱ ሳይሆን እርሱን የሚመስል ሌላ ግለሰብ ነው:: በመሆኑም ኢየሱስ ሳይሞት እንዲሁ ወደ ሰማይ እንዳረገ ቁርአን በተጨማሪ ይናገራል:: በመሆኑም በመጽሐፍ ቅዱስና በቁርአን መካከል ከፍተኛ ተቃርኖ አለ::

በአንጻሩ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ መስቀልና መሞት አስቀድሞ በነቢያት በተተነበየው ትንቢት መሠረት ተሰቅሎ እንደሞተ ያስተምራል (ኢሳ. 53):: ታዲያ መቀበል የሚገባን ኢየሱስ አልተሰቀለም፤ አልሞተም የሚለውን ቁርአን ወይስ ኢየሱስ ተሰቅሎአል፣ ሞቶአል፣ ተቀብሮአል፣ ሞትን ድል አድርጎ በሦስተኛው ቀን ተነሥቶአል፣ ወደ ሰማይም አርጎአል፣ እንደገና ተመልሶ ይመጣል የሚለውን መጽሐፍ ቅዱስ ነው?

## 6.6 እግዚአብሔር ልጅ እንዳልወለደ

*«በል:- እርሱ አላህ አንድ ነው:: አላህ የሁሉ መጠጊያ ነው:: አልወለደም፤ አልተወለደምም»* (ቁርአን ሱረቱ 112÷1-3)::

ቁርአን እግዚአብሔር ማንንም እንዳልወለደና ፈጽሞ ልጅ እንደሌለው ይናገራል:: የእስልምና ሊቃውንትም የቁርአንን ቃል መሠረት በማድረግ እግዚአብሔር ሚስትም ሆነ ወዳጅ፣ እንዲሁም ደግሞ ልጅ የለውም በማለት አጥብቀው ያስተምራሉ::

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ አንድያ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ይናገራል (ዮሐ. 3÷16):: የኢየሱስ ልጅነት የባሕርይ ሲሆን፣ የአማኞች ልጅነት የተገኘው ደግሞ በእግዚአብሔር ጸጋና ምሕረት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ጥርት አድርጎ ያስተምራል:: ታዲያ እግዚአብሔር ፈጽሞ ልጅ የለውም የሚለውን ቁርአንን ወይስ እግዚአብሔር አንድ ብቸኛ ልጅ አለው፤ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው የሚለውን መጽሐፍ ቅዱስን ነው ማመን የሚገባን?



# VII. ሌሎች ነጥቦች

## 7.1 የሲና ተራራ በእስራኤል ሕዝብ ላይ ስለ መንሳፈፉ

*«የጡርን ተራራ ነቅለን ከበላያቸው እንደ ጥላ ኾኖ በአነሳነውና እርሱም በነሱ ላይ ወዳቂ መኾኑን ባረጋገጡ ጊዜ አስታውስ፤ የሰጠናችሁን በብርታት ያዙ»* (ቁርአን ሱረቱ 7÷17)::

ቁርአን የሲና ተራራ (የጡር ተራራ) ከመሬት ተነሥቶ በእስራኤል ልጆች ላይ እንደተንሳፈፈ ይናገራል:: በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ 19÷16-19 በተራራው ላይ ነጎድጓድ፣ መብረቅ፣ እሳት፣ ጢስና ከፍተኛ ድምፅና ርድዔ ምድር በሚመስል መልክ የእግዚአብሔር ሕልውና በሚያርድ ገጽታ እንደተገለጸ ይናገራል:: ሆኖም ተራራው ተነቅሎ በሕዝቡ ላይ ስለ መንሳፈፉ ጉዳይ የሚናገር ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አይገኝም::

እንግዲህ ቁርአን እንዲህ ዓይነቱን አስደናቂ ተአምር ከየት አመጣው? ሰመሆኑ ተራራው ከመሬት ተነሥቶ በሕዝቡ ላይ ቢንሳፈፍ ኖሮ ሕዝቡ ይተርፍ ነበርን? ታዲያ እኛ ማመንና መቀበል የሚገባን መጽሐፍ ቅዱስ የተናገረውን ታሪክ ወይስ ቁርአን ያቀረበውን ነው?

## 7.2 ሕይወት ያለው ሁሉ ከውኃ ስለ መፈጠራቸው

*«አላህ ተንቀሳቃሽን ሁሉ ከውኃ ፈጠረ፤ ከነሱም በሆዱ ላይ የሚሄድ አለለ፤ ከነሱም በሁለት እግሮች ላይ የሚኼድ አለለ፤ ከነሱም በአራት ላይ የሚኼድ አለለ»* (ቁርአን ሱረቱ 24÷45)::

*«እርሱም ያ ከውኃ ሰውን የፈጠረ»* (ቁርአን ሱረቱ 25÷54)::

ሕይወት ያላቸው ፍጥረታት ሁሉ ከውኃ እንደ ተፈጠሩ ቁርአን ይናገራል:: በቁርአን ሱረቱ 21÷30 ያለው የቁርአን አንቀጽም ይህንኑ ርዕሰ ጉዳይ ያጠናክራል:: ስለዚህ *'ተንቀሳቃሽ ሁሉ'* የሚለው መላውን ፍጥረታት ማለት እንደሆነ አይጠረጠርም:: ከእነዚህም መካከል:- በሆዳቸው የሚሳቡ፣ በሁለት እግሮች የሚሄዱና በአራት እግሮች የሚሄዱ ይገኙበታል ይላል ቁርአን:: በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሰው እንኳን ሳይቀር ከውኃ እንደ ተፈጠረ ቁርአን ይናገራል:: ምክንያቱም *'ከነሱም በሁለት እግሮች ላይ የሚኼድ አለለ'* የሚለው ሰውን የሚመለከት ነው::

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ መላው ፍጥረታት በስድስት ቀናት ጊዜ ውስጥ እንደ ተፈጠሩ ይናገራል:: ይህ የሆነበት ምክንያት እግዚአብሔር የሥርዓት አምላክ መሆኑን ለመግለጽ እንጂ ሁሉንም ፍጥረታት ከአንድ ማይክሮ ሴኮንድ ባነሰ ጊዜ ውስጥ ፈጥሮ ማጠናቀቅ አይሳነውም ነበር ይላሉ ክርስቲያን ምሁራን:: እግዚአብሔር በስድስተኛው ቀን ለልዩ ዓላማና ተልዕኮ *'ሰው'* የተሰኘውን ልዩ ፍጥረት በአምሳሉና በመልኩ ፈጠራቸው:: የመጀመሪያው ሰው አዳም የተፈጠረው ከውኃ ሳይሆን ከአፈር እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ዘፍጥ. 2÷7)::

በመሠረቱ ቁርአን ስለ ሰው አፈጣጠር በተመለከተ ከሰብአዊ አእምሮና ግምት በላይ የሆኑ ዝርዝር ነገሮችን አቅርቦአል:: ከእነዚህም መካከል የሚከተሉት ነጥቦች ይገኙበታል፡-

- ሰው ከአፈር ስለ መፈጠሩ (ቁርአን ሱረቱ 3÷59፤ 18÷37፤ 22÷5፤ 30÷20፤ 35÷11)፤
- ሰው ከጭቃ ስለ መፈጠሩ (ቁርአን ሱረቱ 6÷2፤ 7÷12፤ 17÷61፤ 23÷12፤ 3÷27)፤
- ሰው ከሚገማ ጥቁር ጭቃ ስለ መፈጠሩ (ቁርአን ሱረቱ 15÷26, 28, 33)፤
- ሰው ከሚቅጨለጭል ደረቅ ጭቃ ስለ መፈጠሩ (ቁርአን ሱረቱ 55÷14)፤
- ሰው ከረጋ ደም ስለ መፈጠሩ (ቁርአን ሱረቱ 96÷1-2) እና ሌሎችም ነጥቦች በቁርአን ይገኛሉ::

ነገር ግን በአንጻሩ መጽሐፍ ቅዱስ ሰው የተፈጠረው ከአፈር ብቻ እንደ ሆነ ጥርት ባለ ሁኔታ አቅርቦአል (ዘፍጥ. 2÷7):: ሌሎች ፍጥረታት ደግሞ *'ይሁን'* በሚለው አምላካዊ ትእዛዝ እንደ ተፈጠሩ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል:: ታዲያ ስለ ሰው አፈጣጠር በግልፅ ያቀረበው ቁርአን ወይስ መጽሐፍ ቅዱስ ነው? ስለ ጠቅላላው ፍጥረታት አፈጣጠር ሁለቱ መጻሕፍት ያቀረቡት የተለያየ ከሆነ በአርስዎ አመለካከት እውነተኛ ታሪክ የትኛው መጽሐፍ ነው ብለው ያስባሉ?

## 7.3 ሰው ችኩልና ደካማ ሆኖ ስለ መፈጠሩ

*«ሰው ቸኳይ ኾኖ ተፈጠረ»* (ቁርአን ሱረቱ 21÷37)::
*«ሰው ደካማ ሆኖ ተፈጠረ»* (ቁርአን ሱረቱ 31÷28)::

እነዚህ ሁለት የቁርአን አንቀጾች ሰው *'ችኩል'* እና *'ደካማ'* ሆኖ እንደ ተፈጠረ የሚናገሩ ናቸው:: እዚህ ላይ መጠየቅ የሚያስፈልገው፣ *'የትኛው ሰው?'* የሚል ይሆናል:: የመጀመሪያው ሰው አዳም ወይስ ከአዳምና ከሔዋን የተገኙ? ስለ ሰው ስንናገር በሁለት ከፍለን መሆን አለበት:: እነዚህም ከውድቀት በፊትና በኋላ ያለው የሰው ማንነት ለይተን ማወቅ ይኖርብናል:: እነዚህን በትክክል ለይተን ሳናውቅ ስለ ሰው በቂና መሠረታዊ ግንዛቤ ሊኖረን አይችልም:: እስልምና አዳም ኃጢአት መሥራቱን ቢያምንም፣ መልሶ ስለ ተጸጸተ እግዚአብሔር ምሕረት አድርጎለታል በማለት የውርስ ኃጢአት እንደሌለ ያስተምራል:: ይሁንና ግን ሰው ችኩልና ደካማ ሆኖ መፈጠሩን መጽሐፍ ቅዱስ ፈጽሞ አይናገርም:: ከውድቀት በፊት ያለው ሰው ፈጽምና አንከን አልባ ነበር:: ከውድቀት በኋላ ግን የሰው ፈጽምና ተበላሽቶአል፤ ሰውን ችኩልና ደካማ ያደረገው ኃጢአት እንጂ የመጀመሪያው ሰው ሲፈጠር ችኩልና ደካማ ሆኖ አልተፈጠረም::

እንግዲህ ከላይ ያለው የቁርአን አንቀጽ ሰው ችኩልና ደካማ ሆኖ መፈጠሩን ሲያወሳ፣ በሌላ የቁርአን አንቀጽ ደግሞ የሰውን ከፍተኛነት ወይም ከሁሉም ፍጥረታት በላይ ብልጫ እንዳለው ተጠቅሶ ይገኛል (ቁርአን ሱረቱ 17÷70):: ስለሆነም እነዚህ ሁለት የቁርአን አንቀጾች እርስ በርስ እንደሚጋጩ መገንዘብ ይቻላል:: ምክንያቱም ቁርአን ሱረቱ 21÷37 ሰው *ችኩል*፣ ቁርአን ሱረቱ 4÷28



ደግሞ ሰው ደካማ መሆኑን ሲናገርና ሲያረጋግጥ፣ በቁርአን ሱረቱ 17÷70 ደግሞ የሰውን ታላቅነትና ከፍጥረታት ሁሉ በላይ መሆኑን ይናገራል::

ስለሆነም ቁርአን ሰው ደካማና ችኩል ሆኖ ተፈጥሮአል ሲል፣ በአንጻሩ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያው ሰው (አዳምና ሔዋን) አንከን አልባ ሆነው በእግዚአብሔር መልክና አምሳል ተፈጥረዋል፤ ነገር ግን አዳምና ሔዋን በሰይጣን ተንኮል በመታለል ስኃጢአት ከወደቁ በኋላ የሰው ፍጹምና ከኃጢአት የተነሳ ተበላሽቶአል ይላል (2 ቆሮ. 10÷4):: በመሆኑም በኃጢአት ምክንያት አስተሳሰቡና አመለካከቱ ለተበላሸው የሰው ልጅ ሁሉ ዘላቂ የሆነ መፍትሔ ተገኝቶአል ይላል መጽሐፍ ቅዱስ:: መፍትሔውም ደግሞ እግዚአብሔር የላከው ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስን የግል መድኃኒት አድርጎ መቀበል ታላቅ መፍትሔ ነው:: ያለ ኢየሱስ ክርስቶስ ዕርዳታ ሰው ከደካማነትና ከአቅመ ቢስነት ነጻ መውጣት አይችልም:: እንደዚሁም ያለ መለኮታዊ አጋዥነት ወይም ጣልቃ ገቢነት በግል መፍጨርጨርና ጽድቅን በመሻት ብቻ ዘላለማዊ ድነት ወይም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት አይቻልም ይላል - መጽሐፍ ቅዱስ:: ታዲያ ትክክለኛ ታሪክ ያቀረበው ቁርአን ወይስ መጽሐፍ ቅዱስ ነው? ምርጫው የግልዎ ቢሆንም፣ ነገር ግን ሐቀኛ መሆን ይጠበቅብዎታል::

## 7.4 ስለ ነነዌ ከተማ የሕዝብ ብዛት

*«ወደ መቶ ሺህ ሰዎችም (ዳግመኛ) ላክነው፤ ክቶውንም ይጨምራሉ»* (ቁርአን ሱረቱ 37÷147)::

የነነዌ ከተማ ሕዝብ ብዛት አንድ መቶ ሺህ ብቻ እንደነበሩ ቁርአን ይናገራል:: ወደ ነነዌ ከተማ የተላከው ነቢይ ዮናስ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስና ቁርአን ይስማማሉ:: ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ ከቁርአን በተቃራኒ የነነዌ ከተማ ሕዝብ ብዛት ከአንድ መቶ ሃያ ሺህ በላይ እንደሆኑ ይናገራል (ዮናስ 4÷11)::

እንግዲህ ቁርአን የነነዌ ከተማ ሕዝብ ብዛት አንድ መቶ ሺህ ብቻ ናቸው ሲል፣ በአንጻሩ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ የነነዌ ከተማ ሕዝብ ብዛት ከአንድ መቶ ሃያ ሺህ በላይ እንደሆኑ ይናገራል:: ታዲያ የትኛው መጽሐፍ ያቀረበውን ነው እውነት ነው ብለን መቀበልና ማመን የሚገባን? የነነዌ ከተማ ሕዝብ ብዛት አንድ መቶ ሺህ ወይስ ከአንድ መቶ ሃያ ሺህ በላይ?

## 7.5 እግዚአብሔር መላእክትን ስለ መውለዱ

*«አላህ (መላእክትን) ወለደ፤ እነሱም በእርግጥ ውሸታሞች ናቸው (ቁርአን ሱረቱ 37÷152)::*

መጽሐፍ ቅዱስ መላእክት መኖራቸውን እንጂ እንዴት እንደ ተፈጠሩ ምንም ዓይነት መግለጫ ወይም መረጃ አያቀርብም:: ይሁን እንጂ ሁሉን ቻይ የሆነው እግዚአብሔር እንደ ፈጠራቸው አይጠረጠርም:: ይሁንና ግን ቁርአን *'እግዚአብሔር መላእክትን ወለደ'* የሚል ሐሳብ አቅርቦአል:: ሆኖም *'ፈጠረ'* እና *'ወለደ'* በሚሉት ሐረጎች መካከል ከፍተኛ ልዩነት አለ:: ስመሆኑ እግዚአብሔር መላእክትን ከማን

ወሰዳቸው? እንዴትስ ወሰዳቸው? መቼስ ተወሰዱ? የተሟላ መረጃ ያስፈልጋል:: በመሆኑም እግዚአብሔር መላእክትን ወሰደ ሲባል ስፊ ማብራሪያ ያስፈልጋል ማለት ነው::

ከዚህም ባሻገር ቁርአን መላአክት እንደ ተወሰዱ ብቻ ሳይሆን ውሸታሞች መሆናቸውን ጭምር ይናገራል:: ነገር ግን መላእክት ስለ መወሰዳቸውና ውሸታም ስለ መሆናቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አይገኝም:: እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ መሠረት መላእክት በሁለት ይከፈላሉ:: እነርሱም:- ቅዱሳንና ርኩሳን መላእክት ናቸው:: ከርኩሳን መላአክት ባሕርይ አንዱ ውሸታም መሆኑ ነው (ዮሐ. 8÷44)::

እንግዲህ ቁርአን እግዚአብሔር መላእክትን እንደ ወሰዳቸውና እነርሱም ውሸታሞች እንደሆኑ ሲናገር፣ በአንጻሩ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ መላእክት መፈጠራቸውን እንጂ መወሰዳቸውንና ውሸታሞች ስለ መሆናቸውን ምንም አይናገርም:: ታዲያ የትኛው መጽሐፍ ያቀረበውን ነው መቀበልና ማመን የሚገባን? መላእክት ስለ መወሰዳቸውና እነርሱም ውሸታም ስለ መሆናቸው የሚናገረውን ቁርአን ወይስ መላአክት መፈጠራቸውን ብቻ የሚናገረውን መጽሐፍ ቅዱስ ነው?

## 7.6 ምድር በሁለት ቀናት እንደ ተፈጠረ

*«በላቸው:- እናንተ በዚያ ምድርን በሁለት ቀኖች ውስጥ በፈጠረው አምላክ በእርግጥ ትክዳላችሁን?»* (ቁርአን ሱረቱ 41÷9,12)::

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ቀን ምድርን ብቻ ሳይሆን ሰማይንና ምድርን መፍጠሩን ይናገራል (ዘፍጥ. 1÷1):: በመሆኑም ምድር በሁለት ቀን ጊዜ ውስጥ ስለ መፈጠሩ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አናገኝም::

እንግዲህ ቁርአን ምድር በሁለት ቀናት ጊዜ ውስጥ መፈጠሩን ሲናገር፣ በአንጻሩ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ዓይነት ታሪክ አላቀረበም:: ታዲያ ቁርአን ያቀረበውን ታሪክ ነው ማመን የሚገባን ወይስ መጽሐፍ ቅዱስ ያቀረበውን ነው?

## 7.7 ስለ ቃየል፣ አቤልና የቁራ ሚና

*«የወንድሙንም ሬሳ እንዴት እንደሚሸሽግ ያሳየው ዘንድ አላህ መሬትን የሚጭር ቁራን ላከለት፤ ወይ እኔ የወንድሜን ሬሳ አሸሽግ ዘንድ እንደዚህ ቁራ ብጤ መኾን አቃተኝን? አለ፤ ከጸጸተኞችም ኾነ»* (ቁርአን ሱረቱ 5÷31)::

ቁርአን የአቤል አስከሬን አቀባበር በተመለከት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሌለውን አዲስ መገለጥ አቅርቦአል:: ከዚህም የተነሳ ሙስሊም ደራሲ የሆኑት ዓፊፍ ዓብዱልፈታህ ስለ ቁራ ሚና እና ስለ አቤል አስከሬን አቀባበር ሁኔታ በተመለከተ እንዲህ በማለት ተንትነዋል:-

*«ቃየል ወንድሙን አቤልን በገደለው ጊዜ የሚያደርገውን አጥቶ ዋለለ:: አላህ ሁለት ቁራዎችን ላከና አንዱ ቁራ ሌላውን ገደለው:: ከዚያም ገዳዩ ቁራ በምንቃሩ ወይም በእግሮቹ ጫር ጫር አደረገና የገደለውን ቁራ*



*ቀበረው:: ቃየል ቁራው የገደለውን ወገኑን በተመለከተ ጊዜ ከቁራው ያነሰ የርኅራኄ ስሜት ሊኖረኝ አይገባም የሚል ስሜት አደረበት:: ከዚያም በፈፀመው እርኩስ ተግባር በፀፀት እየተቃጠለ የወንድሙን ሬሳ መሬቱን ቆፍሮ ቀበረው:: እንዲህም አለ:- 'በርኅራኄ ከዚህ ቁራ ያነስኩ መሆን ይገባኛልን?'»*[4]

ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 4 ስለ ቃየልና አቤል የሚናገር የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው:: በዚህ ምንባብ ውስጥ ስለ ቁራ ሚና የሚናገር አንድም ቃል አልተጠቀሰም:: እግዚአብሔር የአቤልን መሥዋዕት ሲቀበል፣ በአንጻሩ ደግሞ የቃየልን መሥዋዕት ባለመቀበሉ ምክንያት በቅንዓት ተነሳስቶ ታናሽ ወንድሙን ገደለው:: የአቤልን አስከሬን ማን እንደ ቀበረው መጽሐፍ ቅዱስ ምንም ዓይነት መግለጫ ባይሰጥም እንኳን አዳምና ሔዋን የልጃቸውን አስከሬን እንደ ቀበሩ መገመት ይቻላል:: ስለሆነም እንደ ቁርአን አገላለጽ እግዚአብሔር ሁለት ቁራዎችን ወደ ቃየል ልኮ አንዱ ቁራ ሌላኛውን እንዲገድል አድርጎ በምሳሌ አስተማረውና የወንድሙን አስከሬን ቀበረው የሚል አስተያየት አቅርቦአል - ቁርአን::

እንግዲህ ይህ እንደ አዲስ መገለጥ የሚታይ ከሆነ አጅግ አስገራሚ ይሆናል:: ምክንያቱም ስለ ቁራ ታሪክና ሚና በተመለከተ ስለ አዳም፣ ሔዋን፣ ቃየልና አቤል በሚናገረውና *'ፒርክ ሬቢ እልኤዘር'* በተባለው የአይሁድ አፈ ታሪክ ውስጥ እንደ ተጠቀሰ ምንጮች ይጠቁማሉ:: ታዲያ የቁራ ታሪክና ሚና በአይሁድ አፈ ታሪክ ውስጥ ተጠቅሶ የሚገኝ ከሆነና ቁርአንም ይህንን እንደ አዲስ መገለጥ ወስዶ ካቀረበ እንዴት ይህን ታሪክ እውነት ነው ብለን መቀበል እንችላለን?

## 7.8 መንፈስ ቅዱስ ገብርኤል ስለ መባሉ

*«አላህ በሚል ጊዜ (አስታውስ):- የመርያም ልጅ ዒሳ ሆይ! ባንተና በእናትህ ላይ (የዋልኩላችሁን) ጸጋዬን አስታውስ፤ በሕፃንነትና በከፈኒሳነት (የበሰለ ሰው ኾነህ) ሰዎችን የምትናገር ልትኾን በቅዱስ መንፈስ (ገብርኤል) ባበረታሁህ ጊዜ»* (ቁርአን ሱረቱ 5÷116)::

*መንፈስ ቅዱስ ገብርኤል ስለ መባሉ ቀጥሎ የሚገኙትን የቁርአን አንቀጾች ይመልከቱ* (ቁርአን ሱረቱ 16÷102፤ 19÷17፤ 26÷193፤ 78÷38)::

እንግዲህ የቁርአን ገብርኤል መንፈስ ቅዱስ ሲሆን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ገብርኤል ግን የእግዚአብሔር መልአክ ነው:: በመሆኑም መንፈስ ቅዱስ ገብርኤል ነው የሚለው የቁርአን ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በእጅጉ ይቃረናል:: ሌላው ከላይ በተጠቀሰው የቁርአን አንቀጽ ውስጥ ኢየሱስ በሕፃንነቱ ወቅት እንደ በሰለ (እንደ ትልቅ) ሰው ሰዎችን ያናግር እንደ ነበር ተገልጾአል:: ይህም እንደ ሌሎቹ ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አይገኝም:: ኢየሱስ ሕፃን ሳለ መናገር መቻሉን ቁርአን ተአምርነቱን እንዳቀረበ ቀደም ብለን ማየታችን ይታወሳል::

4. ገድለ ነቢያት በቁርአን ክፍል አንድ፤ ደራሲ ዓፊፍ ዓብዱልፈታህ ጠበራ፤ ትርጉም:- አወል ረታ ሀምሌ 1985 አዲስ አበባ ገጽ 56

ስለዚህ ከላይ ማየት እንደ ሞከርነው ቁርአን መንፈስ ቅዱስ ገብርኤል ነው ሲል፣ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ገብርኤል መንፈስ ቅዱስ ሳይሆን ከብዙ አእላፋት መላእክት መካከል አንዱ መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ነው ይላል። ታዲያ የትኛው መጽሐፍ ያቀረበውን ነው መቀበል የሚገባን?

## 7.9 ሰይጣን ከሰማይ የተጣለው ለአዳም ባለመስገዱ እንደሆነ

*«(አላህም)፡- ኢብሊስ ሆይ ከሰጋጆቹ ጋር የማትኾን ላንተ ምን ምክንያት አለህ አለው፡- ከሚቅጨለጨል ሸክላ ከግም ጭቃ ለፈጠርከው ሰው ልሰግድ አይገባኝም አለ። (አላህ) አለው፡- ከርሷም (ከገነት ወይም ከሰማያት) ውጣ! አንተ የተባረርክ ርጉም ነህና»* (ቁርአን ሱረቱ 15፥32-34)።

እግዚአብሔር ሰይጣንን ለአዳም እንዲሰግድ የጠየቀበት ክፍል በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አይገኝም። ሰይጣን ለአዳም መስገድ እምቢ እንዳለ ተጨማሪ የቁርአን አንቀጾች ይመልከቱ (ቁርአን ሱረቱ 17፥61፤ 18፥50፤ 20፥116፤ 38፥71-76)።

ሰይጣን ከከበረው ከሰማያዊ ሥፍራ የተባረረው ወይም የተጣለው ለአዳም ባለመስገዱ ነው ይላል ቁርአን። በአንጻሩ ሰይጣን ከሰማይ የተጣለው በትዕቢቱና በዐመጹ ምክንያት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል ይናገራል፡-

*«አንተም በልብህ፡- ወደ ሰማይ አርጋለሁ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ በሰሜንም ዳርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ እቀመጣለሁ ከደመናዎች ከፍታ በላይ አርጋለሁ በልዑልም እመሰላለሁ አልህ። ነገር ግን ወደ ሲኦል ወደ ጉድጓድም ጥልቅ ትወርዳለህ»* (ኢሳ 14፥13-15)

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደ ተገለጸው እግዚአብሔር ሰይጣንን ከሰማይ የጣለበት ምክንያት ከፍጡርነት ወደ መለኮትነት የመሸጋገር ጥማት ስለ ነበረው ነው። ነገር ግን እንደ ቁርአን አገላለጽ እግዚአብሔር ሰይጣንን ለአዳም እንዲሰግድ ጠይቆት ነበር ብለን ብናስብና ብናምን እንኳን የሚጠበቀው ውጤት ምንድነው? ብለን መጠየቅ አለብን። በመሠረቱ ስግደት ሚገባው ለሰው ሳይሆን ለእግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ የቁርአን ባለቤቶችም የሚክዱ አይደለም። መታወቅ ያለበት ሰይጣን በመጀመሪያ ሰይጣን ሆኖ አለመፈጠሩ ነው። ሰይጣን በአንድ ወቅት ቅዱስ የእግዚአብሔር መልአክ ነበር። ሰይጣን ማለት የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን፣ ትርጉሙም አለናካይ ማለት ነው። ስለሆነም ሰይጣንን አለናካይ ያደረገው ዐመጹ እንጂ በተፈጥሮው ዐመጸኛ ወይም አለናካይ አልነበረም ማለት ነው (ሕዝ. 28፥15-71)።

እንግዲህ ቁርአን ሰይጣን የተጣለው ለአዳም አልሰግድም ብሎ በማመጹ ምክንያት ነው ሲል፣ በአንጻሩ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ሰይጣን የተጣለው ስትዕቢቱና ከፍጡርነት ወደ መለኮትነት የመሸጋገር ጥማት ስለ ነበረው እግዚአብሔር ከከበረው ከሰማያዊ ሥፍራ ጣለው ይላል። ታዲያ መቀበል የሚገባን ቁርአን ያቀረበውን ወይስ መጽሐፍ ቅዱስ ያቀረበውን ነው?



## 7.10 ዘካርያስ ሦስት ቀንና ሌሊት ብቻ መናገር አለመቻሉ

*«፡- ጌታዬ ሆይ! (እንግዲያስ) ለኔ ምልክትን አድርግልኝ አለ፣ ምልክትህ ጤናማ ሆነህ ሳለህ ሦለት ሌሊትና (ከነቀናቸው) ሰዎችን ለማነጋገር አለመቻልህ ነው አለው»* (ቁርአን ሱረቱ 19፥10)፤ በተጨማሪ ቁርአን ሱረቱ 3፥41 መመልከት ይቻላል።

እንደ ቁርአን አገላለጽ ዘካርያስ (የመጥምቁ ዮሐንስ አባት) ልጅ ስለ ማግኘቱ እግዚአብሔርን ምልክት ይጠይቀዋል። እግዚአብሔርም ለሦስት ቀናት ብቻ ዲዳ (መናገር እንደ ማይችል) ሆኖ እንደሚቆይ ይነግረዋል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ታሪኩ የሚገኘው በሉቃስ 1፥18-19 ላይ ሲሆን፣ ዘዳርያስ ዲዳ ወይም መናገር ያልቻለው መልአኩ ይዞት የመጣውን መለኮታዊ ብሥራት ማመን ባለመቻሉ ምክንያት እንደሆነ ተገልጾአል (ሉቃ. 1፥59-64)። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ ዘካርያስ ዲዳ ሆኖ የቆየው ልጁ (መጥምቁ ዮሐንስ) እስኪወለድ ድረስ ማለትም ለዘጠኝ ወራት ያህል እንጂ ለሦስት ሌሊትና ቀናት አይደለም።

እንግዲህ ቁርአን ዘካርያስ መናገር ያልቻለው ለሦስት ቀንና ሌሊት ብቻ ነው ሲል፣ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ልጁ ማለት መጥምቁ ዮሐንስ እስኪወለድ ድረስ ነው ይላል። ታዲያ ማመንና መቀበል የሚገባን የቁርአንን ወይስ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ ነው?

## 7.11 የሳኦል ሠራዊት በውኃ ስለ መፈተኑ

*«ጧሉትም በሠራዊቱ (ታጅቦ) በመጣ ጊዜ አላህ በወንዝ (ውኃ) ፈታኛችሁ ነው፤ ከርሱም የጠጣ ሰው ከእኔ አይደለም፤ ያልተቀመሰውም ሰው በእጁ መዝገንን የዘገነ ሰው ብቻ ሲቀር እርሱ ከእኔ ጋር ነው አለ፤ ከነርሱም ጥቂቶች ሲቀሩ ጠጡ፤ እርሱና እነዚያም ከርሱ ጋር ያመኑት (ወንዙን) ባለፉት ጊዜ፡- ጃሉትንና ሠራዊቱን በመዋጋት ለኛ ዛሬ ችሎታ የለንም አሉት፤ እነዚያ እነርሱ አላህን ተገናኝዎች መኾናቸውን የሚያረጋግጡት፡- ከጥቂት ጭፍራ በአላህ ፈቃድ ብዙ ጭፍራ ያሸነፈች ብዙ ናት፤ አላህም ከታጋሾች ጋር ነው አሉ»* (ሱረቱ 2፥1-49)።

*'ጧሉት'* ተብሎ በቁርአን የተለየመው የመጀመሪያው የእስራኤል ንጉሥ የነበረው ሳኦል መሆኑን የእስልምና ምሁራን አይክዱም። ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ የንጉሥ ሳኦል ሠራዊት በውኃ ስለ መፈተኑ ምንም ባይናገርም፣ የቁርአን ታሪክ የጌዴዎን ሠራዊት ከተፈተነበት ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ ነው ማለት ይቻላል። ታሪኩም የሚገኘው በመጽሐፈ መሳፍንት ምዕራፍ 7፥4-6 ሲሆን፣ ከንጉሥ ሳኦል ጋር የሚገናኝ ታሪክ አይደለም። *'ጃሉት'* እስራኤልን ለአርባ ቀናት በማስፈራራት ሕዝቡን የተገዳደረ *'ጎልያድ'* ነው። የሳኦልና የጎልያድ ታሪክ በአንድ ላይ መጠቀሱ ትክክል ነው። ሆኖም ከላይ እንደተጠቀሰው እግዚአብሔር የሳኦልን ሠራዊት በውኃ እንደ ፈተነው የሚገልጽ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለም።

በመሳፍንት ዘመን እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ይመራ ዘንድ ጌዴዎንን አስነሳላቸው። በጌዴዎን መሪነት ምድያማውያን እንዲደመሰሱ ጌዴዎን ተዋጊ ሠራዊት እንዲወጡለት አዋጅ አስነገረ። በዚህ መሠረት 32,000 ሰዎች በፈቃዳቸው ወጡለት። እግዚአብሔርም ለጌዴዎን 'ሠራዊቱ በዝቶአልና የፈራና የደነገጠ ወደ ቤቱ ይመለስ!' አለ። ጌዴዎንም ይህንኑ ለሕዝቡ ተናገረ። ከዚያም 22,000 ሰዎች የፈሩና የደነገጡ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ፣ 10,000 ተዋጊ ጀግኖች ያልፈሩና ያልደነገጡ ብቻ ቀሩ።

እግዚአብሔርም 'አሁንም በዝተዋልና ወደ ወንዝ አውርዳቸውና በዚያም እፈትናቸዋለሁ፤ ፈተናውን የሚያልፉ ብቻ ናቸው ከምድያማውያን ጋር የሚዋጉት' ሲል ለጌዴዎን ተናገረ። ፈተናውም ደግሞ 'ውኃ ጠጡ' የሚል ሲሆን፣ እንደ ውሻ በምላሳቸውና ተንበርክከው የጠጡ ፈተናውን የሚወድቁ ሲሆን፣ በእጃቸው ውኃውን ዘግነው የጠጡ ግን ፈተናውን የሚያልፉ ናቸው። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውኃውን በእጃቸው ዘግነው የጠጡት 300 ሰዎች ብቻ ነበሩ። እግዚአብሔር በእነዚህ ብቻ ምድያማውያንን በእጃችሁ አሳልፌ እሰጣለሁ ሲል ቃል ኪዳን ገባላቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን የመሰለ ጣዕም ያለው ታሪክ ያቀርባል። ቁርአን ግን እንዴት አድርጎ ይህን ታሪክ ከሳኦልና ከጎልያድ ጋር እንዳገናኘ አይታወቅም። ታዲያ ሁለቱ መጻሕፍት ያቀረቡት ታሪክ የተለያየ ከሆነ የትኛውን መጽሐፍ ነው ማመንና መቀበል የሚገባን?

## 7.12 ድንግል ማርያም የሙሴና የአሮን እህት ስለ መባሏ

*«የዒምራን ልጅ መርየምን ያችን ብልቷን የጠበቀችውን (ምሳሌ አደረገ)፤ በርሷም ውስጥ ከመንፈሳችን ነፋፍን፤ በጌታው ቃላትና በመጻሕፍቱም አረጋገጠች»* (ቁርአን ሱረቱ 66÷12)።

*«የአሮን እኅት ሆይ! አባትሽ መጥፎ ሰው አልነበረም እናትሽም አመንዝራ አልነበረችም አሉዋት»* (ቁርአን ሱረቱ 19÷28)።

በቁርአን እገላለጽ መሠረት የድንግል ማርያም አባት ዒሚራን ተብሎ ተጠርቶአል፤ ነገር ግን አዲስ ኪዳን የማርያም አባት ማን እንደሆነ አይነግረንም። የሙሴ፣ የአሮንና የማርያም አባት እንበረም እንደሚባል ከመጽሐፍ ቅዱስ እንረዳለን (ዘጸአ. 3÷1፤ 1 ዜና 6÷3)። ምናልባት ዒምራንና እንበረም አንድ ሲሆን እንደሚችል አንዳንድ ምንጮች ይጠቁማሉ። ነገር ግን በቁርአን ድንግል ማርያም የጌታችን የኢየሱስ እናት የሙሴና የአሮን እህት ተደርጋ ቀርባለች። ሆኖም ከድንግል ማርያም አንድ ሺህ ዓመታት ያህል ርቃ የነበረችው ማርያም የሙሴና የአሮን እህት እንደነበረች እናውቃለን (ዘጸአ. 15÷20)። የሆነ ሆኖ የሙሴና የአሮን እህት ማርያም ድንግል ማርያም አይደለችም። የስም ተመሳሳይ ብቻ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በማርያም ስም የሚጠሩ ስምንት ያህል ሴቶች አሉ።

እንግዲህ ቁርአን ድንግል ማርያም የሙሴና የአሮን እህት አድርጎ አቅርቦአል። ለምን እንደሆነ ባይታወቅም ቁርአን ሱረቱ 19÷28 በህዳጉ ሥር እንዲህ የሚል



ተጽፎአል፦ 'የአባትዎ ልጅ ነው፤ የሙሳ ወንድም ሃሩን አይደለም' የሚል ነው። የእኛ ጥያቄ ደግሞ የቁርአን መገለጥ በቀጥታ ከሰማይ በመልአኩ ገብርኤል አማካኝነት ለመሐመድ ወረደ ተብሎ ስለ ሚታመን እግዚአብሔር ነው በህዳጉ ሥር ልዩ ማብራሪያ እንዲጻፍ ወይም እንዲለጥ ያደረገው? ብለን እንጠይቃለን።

ነገር ግን የሙሴና የአሮን እህት የሆነችው ማርያም ከኢየሱስ ልደት በፊት ከአንድ ሺህ ዓመታት ቀደም ብላ የነበረች መሆኗ ይታወቃል። ታዲያ ማመንና መቀበል የሚገባን የቁርአንን ወይስ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ ነው?

እንግዲህ እስካሁን ትኩረት ሰጥተን ማየት የሞከርነው በመጽሐፍ ቅዱስ እና በቁርአን መካከል ያለውን ከፍተኛና ሰፊ ልዩነት ነው። በመሆኑም በቁርአንና በመጽሐፍ ቅዱስ መካከል ያለውን አለመግባባት መጠነኛ ግንዛቤ እንደጨበጣችሁ ተስፋ እናደርጋለን። መጽሐፍ ቅዱስን ከዳር እስከ ዳር ደጋግመን ማንበብ ከቻልን ስለ ቁርአን አንዳች ነገር እንደ ማይናገር ማረጋገጥ እንችላለን። በአንጻሩ ግን ቁርአን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን እንዳለ አካትቶ ይዞአል፤ ቀደም ሲል ማየት እንደሞከርነው ቁርአን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን እልፎ እልፎ ይተርካል እንጂ ወጥ ታሪክ አላቀረበም። ከዚህም በሻገር ቁርአን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሆኑ ከአዋልድና ከአይሁድ መጻሕፍት፣ እንዲሁም ከአይሁድ አፈ ታሪክ እንደ ወሰደ ለመመልከት ችለን ነበር።

በዚህች አነስተኛ መጽሐፍ የተወሰኑ ነጥቦች ብቻ የቀረቡ ቢሆንም፣ በቁርአንና በመጽሐፍ ቅዱስ መካከል በአንድ ርዕስ ጉዳይ ብቻ በርካታ ልዩነቶች አሉ። ለምሳሌ ከእነዚህም መካከል በዚህች መጽሐፍ ያልተጠቀሱ ሌሎች ነጥቦች፦

- ሙሴና የአንድ ያልታወቀ ሰውዬ ጉዞ ጉዳይ (ቁርአን ሱረቱ 18÷60)፤
- የሳባ ንግሥት ኢየሩሳሌም ከመድረሷ በፊት የንግሥቲቱን ዙፋን ከመቅጽበት ወደ ኢየሩሳሌም እንደመጣ (ቁርአን ሱረቱ 27÷38-40)፤
- ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ አዳም ሰው ብቻ እንጂ የመለኮትነት ደረጃ እንደሌለው (ቁርአን ሱረቱ 3÷59)፤
- የእየሱስ ሥላሴን መቃወምና መካድ (ቁርአን ሱረቱ 5÷116)፤
- ኢየሱስ ስለ መሐመድ መምጣት ስለ መተንበዩ (ቁርአን ሱረቱ 6÷16) እና ሌሎችም በርካታ ነጥቦች ናቸው።

በመጽሐፍ ቅዱስና በቁርአን መካከል በአንድ ርዕስ ጉዳይ ልዩነቶች ሲከሰቱ የቻሉት በምን ምክንያት እንደሆነ የቁርአን ባለቤት የሆኑትን የእስልምና ምሁራንን ብንጠይቃቸው፣ መልሳቸው የሚከተለው እንደሚሆን አይጠረጠርም። ይህም፦ 'የክርስትና መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዞአል፤ በሰዋዊ ድርሰትም ተተክቶአል፤ ዋናውና የጠራ መለኮታዊ የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ጥበቃና እንክብካቤ ስላልተደረገለት ጠፍቶአል፤ አሁን እንኳን በክርስቲያኖች እጅ የሚገኘው መጽሐፍ ቅዱስ የተበረዘና የተከለሰ በመሆኑ ከቁርአን ጋር ሲጣጣም አይችልም። ነገር ግን ቁርአን የጠራ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን የምንረዳበት አንዱ መለኪያ እስካሁን

ከፍተኛ ጥበቃ ስለተደረገለት ሳይበረዝና ሳይከለስ ሕልውን ጠብቆ የቆየና የኖረ መለኮታዊ መጽሐፍ ስለሆነ ነው። ስለዚህ የተሳሳተው መጽሐፍ ቅዱስ እንጂ ቁርአን ፈጽሞ አይሳሳትም፤ ደግሞም አልተሳሳተም የሚል ምላሽ እንደሚያቀርቡ የታወቀ ነው።

እንግዲህ የእስልምና ሲቃውንት እምነት፣ አመለካከትና ግምት ይህን የሚመስል ከሆነ ቀጣዩን ጥያቄዎች መጠየቅ አስፈላጊ ይሆናል። እነዚህም፡-

- ከኖህ ልጆች መካከል በጥፋት ውኃ ጊዜ አንዱ ሰጥሞ ሞቶ ሳለ ክርስቲያን ምሁራን ይህን ያስወጡበት ምክንያት ሰምን ምክንያት ይሆን? ከኖህ ልጆች መካከል አንዱ ከሐዲ እንደነበረ አስቀድሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ቢኖር ኖሮ መበረዝ ስለምን አስፈለገ?
- አብርሃም ጣዖታትን ሰባብሮ ስላስወገዳቸው ተከሶ የአገሬው ፍርድ ቤት በእሳት ተቃጥሎ እንዲሞት ፈርዶበት ወይም ወስኖበት፣ እግዚአብሔር በእሳት ከመቃጠል በተአምር አዳነው ተብሎ በመጽሐፍ ቅዱስ ቢጻፍ ኖሮ ይህን አስደናቂ ገድል መበረዝ ሰለ ምን አስፈለገ?
- የሎጥ ሚስት ከግብረ ሰዶማውያን ጋር መሞት ወይም መጥፋት እንደሚገባት የእግዚአብሔር ቅድመ ውሳኔ ሆኖ ሳለ፣ ይህን ታሪክ መበረዝ ወይም ከመጽሐፍ ቅዱስ አውጥቶ በሌላ መተካት ስለ ምን አስፈለገ? ብለን ጥርት ያለ ጥያቄ መጠየቅ እንችላለን።

በአጠቃላይ ቀደም ሲል ለማየት እንደሞከርነው ስለ ሙሴ፣ ስለ አብርሃም፣ ስለ ፈርዖን፣ ስለ ሐማ፣ ስለ ያዕቆብና ልጆቹ፣ እንዲሁም ሰይጣን የተጣለው ለአዳም ባለመስገዱ እንደሆነ . . . ወዘተ አሁን ቁርአን ላይ ባለው መልኩ ቀደም ሲል በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተጽፎ ቢገኝ ኖሮ መበረዙ ስምን አስፈለገ? ብለን የቁርአን ባለቤት የሆኑትን መጠየቅ ይገባል። ክርስቲያኖች እነዚህን ታሪኮች በመበረዛቸውና እውነተኛውን ታሪክ በማዛባት የተጫወቱት ሚና እንዲሁም ያስገኝላቸው ፋይዳ ምን ይሆን? ወይም ደግሞ እነዚህን ታሪኮች ከመጽሐፍ ቅዱስ በማስወጣታቸው ምክንያት የተጠቀሙት ምን ይሆን?

እንግዲህ እነዚህ ጥያቄዎች ወቅታዊና ተገቢ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዞአልና የያዘው ሐሳብ የእግዚአብሔር ቃል አይደለም፤ በአንጻሩ ግን ቁርአን የጠራ የእግዚአብሔር ቃል ነው የተባለበት ምክንያት ግልፅ አይደለም።

**ተፈጸመ**



## ዋቢ መጻሕፍት


1. የ1961 ዓ.ም እትም የአማርኛ ቁርአን፤
2. የ1954 ዓ.ም እትም መጽሐፍ ቅዱስ፤
3. ቁርአን ·በክርስቲያን ዓይን ከኤል ኤም አብደላ የእንግሊዘኛው ትርጉም በአድሪያን ዳልሚዳ፤ ·የአማርኛው ትርጉም በግርማዊ፤ አሣታሚ የስዊድን ፊላደልፊያ ቤተ ክርስቲያን ሚስዮን
4. ገድለ ነቢያት በቁርአን ክፍል አንድ፤ ደራሲ ዓፊፍ ዓብዱልፈታህ ጠበራ፤ ትርጉም፡- አወል ረታ ሀምዛ 1985 አዲስ አበባ የታተመ


ለአስተያየትና ለጥያቄ ከዚህ በታች ባለው አድራሻ መጠቀም ይቻላል!


ከበደ ሞላ
ፖ. ሣ. ቁ 25005
ኮድ 1000
አዲስ አበባ
E-mail: kebe_kebed@yahoo.com

## ከዚህ በፊት በጸሐፊው የታተሙ መጻሕፍት

1. የእስልምና እና የክርስትና መሠረታዊ ልዩነቶች
2. የተዘነጋው ጸጋ
3. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እስልምና እና ስለ መሐመድ ምን ይላል?
4. የቁርአን እና የመጽሐፍ ቅዱስ ልዩነት
5. በርናባስ - እውን ወንጌል ጽፎአልን?